
# አገር አቀፍ
# የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና
# ስትራተጂ



ትምህርት ሚኒስቴር

ነሐሴ 2000

## ራዕይ

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ራዕይ ለአገሪቷ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት አስተዋጽዎ የሚያበረክት ብቁና በሙያው የሚተማመን ዜጋ በማፍራት የህዝቡን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻልና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ድህነትን ማጥፋት ነው፡፡

# ማ ው ጫ


**ገጽ**

1. **መግቢያ**------------------------------------------------------------ 4
1.1 ነባራዊ ሁኔታዎች ------------------------------------------------------ 4
1.2 የፖሊሲ ማዕቀፍ -------------------------------------------------------6
1.3 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሁን ያለበት ሁኔታ-------------------------7
**2. የአገር አቀፍ የቴ/ሙ/ት/ሥ ስትራተጂ ዓላማዎች ------------------------------- 11**
**3. የኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት መርሆዎች-----------------------13**
**4. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ፅንሰ ሃሳባዊ መርሆዎች--------------------15**
4.1 የቴ/ሙ/ት/ሥ ተቋማት የቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ማዕከላት እንዲሆኑ ማድረግ-------------- 15
4.2 የተቀናጀና የተዋሃደ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት መፍጠርን ኢላማ ማድረግ---------------- 16
4.3 የባለድርሻዎች ተሳትፎ ------------------------------------------------ 19
4.4 የግሉ ዘርፍና የመንግሥት ሽርክና ------------------------------------------ 20
4.5 ውጤትን መሠረት ያደረገ ሥልጠና---------------------------------------------- 22
4.6 ያልተማከለ አሠራር ----------------------------------------------------- 24
4.7 ቀልጣፋ አሠራር በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ----------------------------- 26
**5. ውጤትን መሠረት ላደረገ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማዊ ብቃትን ማሳደግ------ 27**
5.1 የሙያ ደረጃ ምደባ ዝግጅት ------------------------------------------------ 29
5.2 የሙያ ብቃት ምዘናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ -------------------------------- 30
5.3 የኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ብቃት ማዕቀፍ ----------------------- 32
**6. ተለማጭ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ ሥርዓትን ዝርጋታ ------------------ 33**
6.1 ሞጁላራዊ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥን እንደመርህ መከተል--------------------34
6.2 ከኩባንያዎች ጋር በትብብር የሚሰጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና --------------------35
6.3 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ለራስ ሥራ ፈጠራ ------------------------------ 36
6.4 በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን ሥራ ላይ ማዋል ------------------------------37
6.5 የሙያ ምክርና ድጋፍ ---------------------------------------------------- 38
**7. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን አቅም መገንባት ------------------------ 39**
7.1 የመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን ማጠናከር -------------------- 39
7.2 የግል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን ማጠናከር ------------------------41
7.3 የሥርዓት ትምህርት እና መሣሪያዎች ዝግጅት--------------------------------------- 42
**8. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት እውቅና አሰጣጥ ----------------------------43**
**9. የሰው ኃይል ልማት ------------------------------------------------------ 45**
9.1 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራን የቅድመ ሥራ እና ተከታታይ ሥልጠና--------45
9.2 ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስተዳደር የሰው ኃይል ልማት ----------------------47
9.3 ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሠራተኞች አመቺ የሥራሁኔታን መፍጠር------------------ 48
**10. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የፋይናንስ ሥልት --------------------------- 48**
**11. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ምርምር ክትትልና ግምገማ ------------------------ 51**
11.1 የጥናትና ምርምር አቅምን መገንባት -------------------------------------------51
11.2 የሥራ ገበያ ክትትልና ትንበያ ----------------------------------------------52
11.3 የሥራ አመራር መረጃ ሥርዓት --------------------------------------------------53
11.4 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ማሻሻያ ክትትልና ግምገማ --------------------- 54
**12. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስተዳደርና ሥራ አመራር ሥርዓት ----------------------- 54**
**13. ስለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ግንዛቤ መፍጠር ------------------------------- 61**
**14. የዓለም አቀፍ ትብብር ሥራ አመራር ------------------------------------------ 62**

# 1. መግቢያ

1.0.1 ይህ አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራተጂ ቀደም ሲል እ.ኤ.አ በ2002 የተዘጋጀውን ስትራተጂ የሚተካ ነው፡፡ ስትራተጂው በቅርብ ዓመታት የተከሰቱትን መሠረታዊ ለውጦች ከማንጸባረቁም ባሻገር ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥራትና አግባብነት የቅድሚያ ትኩረት ይሰጣል ፡፡ ዓለምአቀፍ ተሞክሮ እንደሚያሳየው የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናን አቅርቦት ማስፋፋት ብቻውን ሥራ አጥነትንና ዝቅተኛ የኢኮኖሚ ምርታማነት ችግርን መቅረፍ አይችልም። በመሆኑም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ገበያው የሚፈልገውን ብቃት ያለው፣ ተነሳሽነትን የተላበሰና ከስራው ፍላጐት ጋር ራሱን የሚያስማማ ብሎም የኢኮኖሚውን ዕድገትና ልማት የሚያራምድ የሰው ኃይል መፍጠር ይኖርበታል፡፡

1.0.2 ይህ ስትራተጂ የተዘጋጀው የመንግስትንና የግሉን ዘርፍ ባለድርሻዎች በስፋት በማሳተፍ ነው፡፡ ስትራተጂው በሚቀጥሉት ዓመታት የሚኖረውን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅጣጫ ዋና ዋና መርሆዎች ይገልፃል፡፡ የስትራተጂው መሠረታዊ መነሻ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዕድገት የሚመሠረተው ብቃት ላይ የተመሠረተ ሥርዓት በመዘርጋት በመንግስትና በግሉ ዘርፍ መካከል በሚኖረው ጠንካራ አጋርነትና በባለድርሻዎች መካከል በሚኖረው ቁርጠኛና መተማመን የተሞላበት ትብብር እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡

## 1.1 ነባራዊ ሁኔታዎች

1.1.1 ኢትዮጵያ በዓለም ካሉት የመጨረሻ ድኃ ሀገሮች ውስጥ አንዷ ናት፡፡ከሕዝቧ ውስጥ ወደ 31 ሚሊዮን የሚጠጋው ከድህነት ወለል በታች የሚኖር ማለትም የቀን ነፍስ-ወከፍ ገቢው 45 የአሜሪካን ሳንቲም ሲሆን በጥቂት ሚሊዮኖች የሚቆጠር ህዝብም በየዓመቱ ለረሃብ አደጋ የተጋለጠ ነው፡፡ ምንም እንኳን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ መሠረታዊ የኑሮ ሁኔታን በማሻሻል ረገድ አበረታች ውጤት ቢመዘገብም ከሌላው የዓለም ክፍል ጋር ሲነጻፀር የሰው ኃይል ልማት አመልካቾች አሁንም ዝቅተኛ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት በየዓመቱ በ2 ሚሊዮን ያህል የሚጨምር ሲሆን፣ ይህም አገሪቷ ባላት የሀብት መሠረት፣ በተፈላጊ አገልግሎቶች አቅርቦትና በሰው ኃይል ገበያ ላይ ከፍተኛ ጫና አሳድሯል፡፡ በአገሪቷ ሁለተኛው የድህነት ቅነሳ ስትራተጂ በፈጣንና ዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ዕቅድ ላይ እንደተጠቀሰው ኢትዮጵያ የምእተ አመቱ የልማት ግብ ለማሳካት በአማካይ በየዓመቱ 8 በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ እንደሚኖርባት ይገመታል፡፡

1.1.2 ኢትዮጵያ በገጠር ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚ ያላት አገር ናት። ዓለም አቀፍ አመላካቾች አንጻር ሲታይ የከተማ ልማት ደረጃ እጅግ በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ከአጠቃላይ ህዝቧ 85 በመቶውና 90 በመቶው ድሃው የህብረተሰብ ክፍል የሚኖረው በገጠር ሲሆን አብዛኛው የተሰማራው በግብርና ላይ ነው፡፡ ምንም እንኳን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አበረታች ውጤት ቢመዘገብም በግሉ ዘርፍ አዝጋሚ ዕድገት ምክንያት ዘመናዊው የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፍ የሚፈለገውን የስራ ዕድል ሊፈጥር አልቻለም፡፡ የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ሰፊ መሠረት የሌለውና መሠረት ያደረገው በምግብ፣ በመጠጥና ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪዎች ላይ ሲሆን እነዚህም ከአጠቃላይ የአገሪቱ የኢንዱስትሪ ምርት ከግማሽ እጅ በላይ ድርሻ አላቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል ከተመዘገቡት አነስተኛና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 85 በመቶው የዱቄት ወፍጮዎች ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ የተመዘገቡት ፋብሪካዎች ማለትም 800 ያህሉ ትላልቅና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የሚገኙት በአዲስ አበባ ነው፡፡ ምንም እንኳ ድርሻው እየጨመረ ቢሆንም ካሉት ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች መካከል እ.ኤ.አ. እስከ 2002/03 ድረስ የግሉ ዘርፍ ድርሻ 27 በመቶ ብቻ ነበር፡፡

1.1.3 35 ሚሊዮን የሚጠጋው የአገሪቷ ሠራተኛ ሃይል በአማካይ በትምህርት ደረጃውና በምርታማነቱ እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ ከከተማው ህዝብ የድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የተከታተለው 10 በመቶው ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም 75% የሚሆነው የስራ ሀይል በዝቅተኛ የሙያ ዘርፎች ማለትም በንግድ፣ በአገልግሎትና በአነስተኛ ስራዎች ላይ ተሰማርቶ ይገኛል፡፡ ከከተማው ህዝብ በምንዳ ቅጥር የሚተዳደረው ግማሽ ያህል የማይሆን ሲሆን የማይናቅ ቁጥር ያለው የስራ ሃይል ደመወዝ በማይከፈልበት የቤተሰብ ስራ ላይ ተሰማርቶ ይገኛል፡፡ ከ40 በመቶ በላይ የሚሆኑት በራሳቸው አነስተኛ ስራ የሚተዳደሩ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ አብዛኛዎቹ በድህነት አፋፍ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡

1.1.4 ኢኮኖሚውን ለማንቀሳቀስ ብቃት ያለው የግሉ ዘርፍ በሌለበት በአሁኑ ወቅት የስራ አጥነትና ከፊል ስራ አጥነት ችግር በስፋት ይታያል፡፡ በገጠርም ከፊል ስራ አጥነት ተስፋፍቶ ይገኛል፡፡ በከተሞች አካባቢ 26 በመቶ የሚሆነው መስራት የሚችል የሰው ሃይል በስራአጥነት ተመዝግቦ የሚገኝ ሲሆን፣ ይህም አጎዝ ከተጨባጭ የችግሩ ስፋት አንፃር ሲታይ ግምቱ ዝቅተኛ ነው፡፡ ችግሩን ይበልጥ አሳሳቢ የሚያደርገው የወጣት ሥራ አጥነት ችግር ከሌሎች ሥራ አጥ የህብረተሰብ ክፍሎች ቁጥር አንጻር ሲታይ በጣም ከፍተኛ መሆኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በቅርቡ የተካሄዱት ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በሁሉም የኤኮኖሚ ዘርፎች በተለይም ከአዲስ አበባ ውጪ እና ከፍተኛ የብቃት ደረጃ በሚጠይቁ የኢኮኖሚ ዘርፎች የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት መኖሩ ነው፡፡

## 1.2 የፖሊሲ ማዕቀፍ

1.2.1 የኢትዮጵያ መንግሥት ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ሲባል የፈጣንና ዘላቂ ኢኮኖሚ ዕድገትና ድህነትን የማስወገድ ዕቅድ፣ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጂንና ሌሎች የልማት ስትራተጂዎችን ቀይሷል፡፡ በእነዚህ ጥረቶች ውስጥ በአጠቃላይ አቅም ግንባታና የሰው ኃይል ካፒታል ፈጠራ የስትራተጂዎቹ ቁልፍ ምሶሶዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ይህ አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራተጂ ባጠቃላይ የኤኮኖሚ ዕድገትና ድህነትን የማስወገድ ፖሊሲ ማዕቀፍ ቁልፍ አካል ነው፡፡

1.2.2 የፈጣንና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገትና ድህነትን የማስወገድ ዕቅድ ዋናው ትኩረት ግብርናን ግብይታዊ ማድረግ እና የግሉን ዘርፍ በማጠናከር የኢኮኖሚውን እድገት ማፋጠን፣ ድህነትን መዋጋትና የሥራ እድልን መፍጠር ነው፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተግባራዊ ክህሎትን የተላበሰ፣ ተነሳሽነትና ብቃት ያለው ተፈላጊ የሰው ኃይል በማፍራት ለዚህ ስትራተጂ ስኬት ቁልፍ ሚና እንዲጫወት ይጠበቃል። በፈጣን፣ ዘላቂ ልማትና ድህነትን የማስወገድ ዕቅድ መሠረት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዓላማ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፎች ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ትምህርትና ሥልጠና በመስጠት ዜጎች በቀጥር የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ወይም ሥራን ራሳቸው እንዲፈጥሩ ማስቻል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ስትራተጂው በትምህርት አገልግሎት አቅርቦት ውስጥ የግሉን ዘርፍ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና የህብረተሰቡን ሚናና ተሳትፎን በማሳደግ አስፈላጊነት ላይ ያተኩራል፡፡ እያደገ የሚሄደውን የሥልጠና ፍላጎት ካለው ውስን ሀብት ጋር ለማመጣጠን የሥራ ቅልጥፍናንና የወጪ ቁጠባ ዘዴዎችን የመጠቀም አስፈላጊነትም ተመልክቷል፡፡

1.2.3 እ.ኤ.አ በ2003 የተቀረጸው የአገሪቷ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጂ ለአገሪቷ የኢንዱስትሪ ዕድገት ዝቅተኛ መሆን የሠለጠነ የሰው ሐይል እጥረት ዋና መንስዔ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም የስትራተጂ ዶክሜንቱ አገሪቷ ከሙያም ሆነ ከሥነ ምግባር አንጻር ብቃት ያለውና የኢንዱስትሪ ዕድገት ግቦችን በዘላቂነት ሊያሳካ የሚችል የሰው ኃይል የሚፈጥር የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት እንዳልነበረ አስምሮበታል። በመሆኑም የአገሪቷን የሠራተኛ ኃይል ጥራት ወደ ዓለም አቀፍ ደረጃ ለማሳደግ፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ ትኩረት ተነፍጎት በቆየው የኢንዱስትሪ ሙያ ላይ ለማተኮር፣ የታታሪነት ባህልና ሥራ ፈጠራን ለማዳበር ከፍተኛ ጥረት መደረግ እንዳለበት ይጠቁሟል፡፡

1.2.4 እ.ኤ.አ በ2005 / 2006 የተነደፈው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም (ESDP) III የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍን አጠቃላይ የዕድገት ራዕይ አስቀምጧል። በተደረገው የዘርፉ ትንተና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ምሩቃን የኢኮኖሚ ዘርፎች የሚጠብቁትንና የሚፈልጉትን በመካከለኛ ደረጃ የሠለጠነ ሰው ኃይል የሚያፈሩ ሆነው አልተገኙም፡፡ ስለሆነም የስትራተጂ ጽሑፉ መደበኛና መደበኛ ያልሆነ የመጀመሪያና ተከታታይ ሥልጠናን እንዲሁም በብቃት ላይ የተመሠረተ የሥልጠና ማስረጃዎች አሰጣጥንና ከከፍተኛ ትምህርት ሥርዓት ጋር ያለውን ጉናዊና አምዳዊ ተያያዥነት በግልጽ ያስቀመጠ ውሁድ ሥርዓት መዘርጋት እንደሚገባ ያስቀምጣል። በትምህርቱ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም III በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቅበላን ለማሳደግ፣ ጥራትን ለማስጠበቅና ለማጠናከር፣ የሥልጠና ዘዴን ለማሻሻል፣ ፊዚካል ኢንፍራስትራክቸርን ለመገንባት፣ መሣሪያዎችን ለመግዛት፣ የሥልጠና ቁሳቁሶችን ለማሟላት፣ አብያተ መጻሕፍትንና የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን ለመገንባት፣ የክህሎት ምዘና ማዕከላትን ለማቋቋም፣ ሥርዓተ ትምህርቶችንና የመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍትን ለመከለስና ለሌሎች ተዛማጅ የኢንቨስትመንት ሥራዎች በጠቅላላው ብር 3000 ሚሊዮን ተመድቧል፡፡ በግብርናም ሆነ ከግብርና ሥራ ውጪ ተሠማርተው ለሚገኙ ለገጠሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን የፋይናንስ አቅም አስተማማኝ ለማድረግ፣ የተቋማቱን አመራር ለማሻሻልና በትምህርትና ሥልጠና ዕቅድ ዝግጅት፣ ሥራ አመራርና ትምህርት አሰጣጥ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ለማሳተፍ የሚያስችሉ መንገዶች ተቀይሰዋል፡፡ ስለሆነም የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም III የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን በአገሪቷ የበለጠ ለማሳደግ የሚያስችሉ ወሳኝ አውታሮችን የዳሰሰ ነው፡፡

## 1.3 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሁን ያለበት ሁኔታ

1.3.1 በኢትዮጵያ በተለምዶ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በተበጣጠሰ ሁኔታ በተለያየ ደረጃ በተለያዩ ተቋሚት ወጥነት በሌለው መልክ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ በትምህርቱ ዘርፍ ሥር የነበሩት የመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚያተኩሩት 10ኛ ክፍል ያጠናቀቁ የመካከለኛ ደረጃ የቴክኒክ ባለሙያዎችን በማፍራት ነበር፡፡ ከነዚህ ተቋማት በተጓዳኝ መንግሥታዊና የግል አምራችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የራሳቸውን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም የሚያካሂዱ ሲሆን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና በርካታ የግል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ይሰጣሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መደበኛ ባልሆነ የቴክኒክና ሙያ

ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም መንግስታዊ ተቋማት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል ትምህርት ቤቶች በስራ ላይ ያሉትን፣ ከትምህርት ቤት ጨርሰው ወይም አቋርጠው የወጡና ሌሎች ስራ አጦችን ጨምሮ በተለያዩ ምክንያቶች ከሥራው ገበያ ለተገለሉ ቡድኖች የሙያ ሥልጠና ይሰጣሉ፡፡ እነዚህ ኘሮግራሞች እንደ መደበኛው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ባለው መንገድ የተመዘገቡ አይደሉም፡፡ መደበኛ ያልሆነ የስራ ላይ ሥልጠና ተስፋፍቶ የሚገኝ ቢሆንም የተቀናጀ የክህሎት ምዘናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓት ባለመኖሩ ባሁኑ ጊዜ ሙያን መሠረት ያደረገው ይህ ሥልጠና ዕውቅና የሚያገኝበት አሠራር የለም፡፡ በጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ስራ ዘርፎች የሚሰጡ ልማዳዊ የስራ ላይ ሥልጠናዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚያበረክቱ ቢሆንም በዚህ የሥልጠና አይነት የተካሄደ ጥናት የለም። በአስተዳደርና በጤና በቂ ባለሙያዎችን ለማፍራት በመንግሥትና በግል ተቋማት የሚሰጡ ሥልጠናዎች በተለይ በእነዚህ ዘርፎች የሰለጠነ የሰው ሐይል የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ ከቅርብ አመታት ወዲህ በስፋት በመካሄድ ላይ የሚገኘው የግብርና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ከሌሎች ግብርና ነክ ካልሆኑ መርሐ ግበሮች ጋር በቅንጅት እየተካሄደ አይደለም፡፡

1.3.2 በየጊዜው ትምህርታቸውን ጨርሰው ለሚወጡ በርካታ ተማሪዎች አማራጭ የስራ ዕድሎችን ለመፍጠር መንግሥት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን በብዛት እያስፋፋ ይገኛል፡፡እ.ኤ.አ ከ1996 /97 እስከ 2004 /5 ባሉት ጊዜያት ግብርና ነክ ያልሆኑ መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሚሰጡ ተቋማት ቁጥር ከ17 ወደ 199 ያደገ ሲሆን፣ የተማሪዎች ቁጥርም በተመሳሳይ ጊዜ ከ3,000 ወደ 106,300 ከፍ ብሏል፡፡ ከነዚሁ ውስጥ 31 በመቶ ያህሉ የሰለጠኑት መንግስታዊ ባልሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ነው፡፡ 60 በመቶ የሚሆነው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሚሰጠው በመደበኛ ፕሮግራም ሲሆን ቀሪው 40 በመቶ ደግሞ በምሽት የተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ነው፡፡ ምንም እንኳን ተቋማቱ በብዛት የተስፋፉ ቢሆንም እስካሁን ድረስ መደበኛዎቹ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚሸፍኑት ትምህርትና ሥልጠናውን ለማግኘት ዕድሜያቸው ከሚፈቅድላቸው ወጣቶች መካከል 3 በመቶ ያህሉን ብቻ ነው፡፡ በመደበኛ የቴክኒክና የሙያ ትምህርትና ሥልጠና ከሚሳተፉ ውስጥ 51 በመቶው ሴት ተማሪዎች በመሆናቸው የተመጣጠነ የፆታ ተሳትፎ ይታያል፡፡ ሆኖም ሴቶች በብዛት እየሠለጠኑ ያሉት በንግድ ሥራ፣ እንደ ጨርቃ ጨርቅና መስተንግዶ በመሳሰሉት በተለምዶ የሴቶች ሥራ ተደርገው በሚቆጠሩ ሙያዎች ሲሆን፣ በሌሎች የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናዎች ተሳትፎአቸው አነስተኛ ነው፡፡ እ.ኤ.አ በ2004 /05 ሌሎች 42,000 የሚሆኑ ሠልጣኞች በግብርና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም የተሳተፉ ሲሆን፣ ሌሎች

10,000 ሠልጣኞች ደግሞ በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማትና ኮሌጆች ተመዝግበው ትምህርትና ሥልጠናቸውን በመከታተል ላይ ነበሩ፡፡

1.3.3 እስካሁን ድረስ በመደበኛ፣ መደበኛ ባልሆነና በኢ-መደበኛ (Formal, Non formal & Informal) ፕሮግራሞች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዕድል ያገኙ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ስንት እንደሆነ በትክክል ለማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡ ሆኖም በአሁኑ ጊዜ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፍላጎቱ ከአቅርቦቱ በላይ መሆኑና አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ የትምህርትና ሥልጠናውን ዕድል እንዳላገኘ ታሳቢ ማድረግ ይቻላል፡፡ በተለይም ትምህርታቸውን ለሚያቋርጡ፣ ለሥራ አጦች፣ ለፋብሪካ ሠራተኞችና በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ለሚሰሩ፣ ሥራን የመፍጠር ተሰጥዎ ላላቸው፣ በገጠር ለሚኖሩ ሰዎችና ለሴቶች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅርቦት እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡

1.3.4 አገሪቷ የሠለጠኑ የእጅ ባለሙያዎችና ቴክኒሽያኖች እንደሚያስፈልጓትና በዚህ ረገድ የሚሰጠው የሥልጠና ፕሮግራም ኋላ ቀርና ካለው የስራ ሁኔታ ጋር ያልተዛመደ መሆኑን በመረዳት መንግስት እ.ኤ.አ ከ1990ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስርዓትን ለማሻሻል ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ሆኖም ግን የማሻሻያ ሂደቱ አዝጋሚና በመንግሥት የቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ተቋማት ቁጥር መጨመር ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ በመምህራንና በሌሎች የሥልጠና ግብዓቶች ዕጥረት ምክንያት የሚሰጡት የሥልጠና ፕሮግራሞች ጥራታቸውን ያልጠበቁና ንድፈ ሃሳብ ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ኢኮኖሚው የሚፈልገውን የሰለጠነ የሰው ሃይል ፍላጎት የሚያሟሉ ሆነው አልተገኙም፡፡ በመሆኑም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን ከተጨባጩ የስራ ዓለም ጋር የማጣጣሙ ጥረት ገና አልተሳካም፡፡ በመደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ስራ ላይ የዋሉት አብዛኛዎቹ ሥርዓተ ትምህርቶችም የሙያ ደረጃን መሰረት አድርገው ያልተቀረጹ ነበሩ፡፡

1.3.5 በአዲሱ የመካከለኛ ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ሰልጣኞች ከኢንዱስትሪ ጋር የሚተዋወቁበት ስልት በተለይ በመደበኛው ፕሮግራም ውስጥ ተካቷል፡፡ ስለ ፕሮግራሙ በአሰሪ ድርጅቶች በቂ ግንዛቤ ባለመኖሩና በዕቅድ ዝግጅት ሂደትም እንዲሳተፉበት ስላልተደረገ በአፈጻጸሙ ላይ በርካታ ችግሮች አጋጥመውታል፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥራትን ለማሳደግና ምሩቃኑም የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ለማድረግ በተቋማቱና በአሰሪ ድርጅቶች ጠንካራ መተጋገዝ ላይ የተመሠረተ

የትብብር ሥልጠናና የሥራ ላይ ልምምድ አሰጣጥ ሥርዓት የሚዘረጋበት መንገድ መቀየስ ይኖርበታል፡፡

1.3.6 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናው ውጤታማና ቀልጣፋ ያለመሆኑን የሚጠቁሙ ሁኔታዎችም አሉ፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በገበያ ላይ በጣም ተፈላጊ በሆኑ ሙያዎች ጭምር የሰለጠኑ በርካታ ተመራቂዎች ሳይቀጠሩ ቀርተዋል፡፡ በተጨማሪም ለመንግስት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በከፍተኛ የኢንቨስትመንት ወጪ የተገዙ መሣሪያዎች በሙሉ አቅማቸው ሥራ ላይ ስለማይውሉ የሃብት ብክነት ታይቷል፡፡

1.3.7 በቂ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራን ክምችት አለመኖር ሌላው ለኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዕድገት አንዱ ማነቆ ሆኖ የቆየ ነው፡፡ ለሙያው በሚሰጠው ዝቅተኛ ግምት ምክንያት ለአገሪቱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የመምህራን አቅርቦትና ያሉትም ቢሆኑ የብቃት ደረጃቸው አነስተኛ ነው፡፡ የአብዛኛዎቹ መምህራን የመደበኛ ትምህርት ዝግጅት ደረጃ በአንጻራዊ መልኩ ዝቅተኛ መሆኑ በከፍተኛ ደረጃ በሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናዎች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል፡፡ በተጨማሪም የቴክኒክ መምህራንን የሚያበረታታ ሁኔታ የለም። መምህራኑ በዝንባሌያቸው ተመርጠው ሳይሆን ሌላ አማራጭ ስለሌላቸው ብቻ በቴክኒክ መምህራን ኮሌጅ ገብተው እንዲሰለጥኑ የተደረጉ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አሁን ያሉት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራን ተገቢውን የተግባር ክህሎት ያልቀሰሙ በመሆኑ በስራው ዓለም በሚፈለገው የሙያ ደረጃ መሠረት ሥልጠና ለመስጠት ብቃት ያንሳቸዋል፡፡ ይህ ችግር ተግባራዊ ክህሎትንና የሥራ ዓለምን ያላገናዘበ እንዲሁም ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጋር ባልተጣጣመ የንድፈ ሃሳብ ትምህርት ላይ ያተኮረ የሥልጠና ሥርዓት ውጤት ነው፡፡

1.3.8 ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ በተለይም ለመንግሥታዊ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚመደበው መዋዕለ ንዋይ አነስተኛነት አንዱ ሥር የሰደደ ችግር ነው፡፡ በኢትዮጵያ እንደተለመደው ሥልጠና የሚሰጠው የሥልጠና ማዕከላትን መሰረት አድርጎ ብቻ ከሆነ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ወጪ ከፍተኛ መሆኑ ይቀጥላል፡፡ እንደሌሎች ብዙ አገሮች ሁሉ በኢትዮጵያም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ወጪ ከአጠቃላይ ትምህርት ወጪ ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም የመምህራንና ተማሪ ጥምርታ ዝቅተኛ ከመሆኑም ባሻገር ለተግባር ሥልጠና የሚያስፈልገው መደበኛና ካፒታል ወጪ ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በዋና ከተሞች

አካባቢ የሚገኙ የማሠልጠኛ ተቋማት በገጠር አካባቢ ከሚገኙት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ የበጀት እጥረት ስላለባቸው የፋሲሊቲና የሥልጠና ቁሳቁሶች አቅርቦት እጥረት የሚታይባቸው ናቸው።

1.3.9 ከላይ የተጠቀሱት በርካታ ሥር የሰደዱ ችግሮች ቢኖሩም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተለይም እ.ኤ.አ በ2002 የወጣውን አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራተጂና እ.ኤ.አ በ2004 የወጣውን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አዋጅ ተከትሎ አንዳንድ ጠቃሚ የማሻሻያ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ በዚህ ረገድ ከሚጠቀሱት ውስጥ የክልል መንግስታዊ ተወካዮችን ጨምሮ ከተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት፣ የመንግስትና የግል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪዎች፣ እንዲሁም የንግዱን ህብረተሰብ ያቀፈ አገርአቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስል በማቋቋም የአስተዳደር መዋቅሩን ለማስፋት የተወሰደው እርምጃ ይገኝበታል፡፡ ይህም እርምጃ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ተቋማዊ በሆነ መልኩ መሳተፍ መጀመራቸውን የሚያመለክትና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ልማት ሥር እንዲሰድና መጠነኛ ግንዛቤ እንዲያገኝ እገዛ ያደረገ ነው፡፡ በመሆኑም ከአዲሱ ሥርዓት ለውጥ ጥረት ጎን ለጎን ይህንን አስተዳደራዊ መዋቅር የበለጠ ማጠናከር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

1.3.10 ሌላው የተወሰደ ጠቃሚ እርምጃ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ አዲሱን የጥራት ማኔጅመንት ሥርዓት ንድፈ ሃሳብ ማስረጽና ተግባራዊ ማድረግ መጀመር ነው፡፡ ዓለም አቀፍ መልካም ተሞክሮዎችን መሰረት በማድረግ አሁን ካለው ስርዓተ ትምህርት ተኮር አሠራር የሙያ ደረጃን መሠረት ወዳደረገ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ለመሸጋገርና የሙያ ደረጃ ብቃት መመዘኛ ሥርዓትን በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑ እንዲሁም በኢ-መደበኛ (Informal) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች ለሁሉም ተመራቂዎችና ዕጩ ተፈታኞች ክፍት ለማድረግ ተወስኖ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡ የሙያ ደረጃን መሰረት ያደረገ የሥልጠና ስርዓትን ከሙያ ምዘናና ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ጋር በማቆራኘት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን አግባብነት ያለው፣ ፍላጎት ተኮርና ለሁሉም እንዲዳረስ የማድረጉ ተግባር የሥርዓት ለውጥ ፕሮግራሙ ቁልፍ ስራ ነው፡፡ በመሆኑም ለሁሉም ባለድርሻዎች ንድፈ ሃሳቡን ማስረጽና አፈጻጸሙን ይበልጥ ማፋጠን ያስፈልጋል፡፡

# 2. የአገርአቀፍ የቴ/ሙ/ት/ሥ ስትራተጂ አላማዎች

2.0.1 የዚህ አገር አቀፍ የቴ/ሙ/ት/ሥ ስትራተጂ አጠቃላይ አላማ በሃገሪቷ ብቁ፣ ተነሳሽነትና የፈጠራ ክህሎት ያለው የሰራተኛ ሃይል በመፍጠር በሃገሪቷ የድህነትን

ማስወገድና ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት አስተዋጽኦ ማድረግ ነው፡፡ ይህም የሚተገበረው በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች ፍላጎት ላይ የተመሰረተና ከፍተኛ ጥራት ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በሁሉም ደረጃ ክህሎታቸውን ለማዳበር ለሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ በማመቻቸት ነው፡፡

2.0.2 የአገርአቀፍ የቴ/ሙ/ት/ሥ ስትራቴጂ ዝርዝር አላማዎች

- በአገሪቷ የተቀናጀ፣ የተዋሃደ በውጤት ላይ የተመሰረተና ያልተማከለ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስርአትን መፍጠርና ማጠናከር፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ማእከል የሚሆኑበትን አሰራር ማጠናከር፣
- ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስርአት ሁሉም ተዋናዮችና ባለድርሻዎች የተቀናጀ የአሰራር ማዕቀፍ መፍጠር፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን ለመፈፀም፣ በብቃት ለመምራትና የጥራት ማኔጅመንት ስርአትን ተግባራዊነት ለማረጋገጥ ተገቢውን ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠርና ማጠናከር፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን (መደበኛውንና መደበኛ ያልሆነውን) ጥራት በሁሉም ደረጃ ማሻሻልና ከስራ ገበያው ፍላጎት ጋር ማጣጣም፣
- ለአገር እድገት ቁልፍ ሚና ባላቸው የስራ መስኮች አግባብነት ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሚዳረስበትን መንገድ ማመቻቸት ፣
- የግሉን የሥልጠና ገበያ ማጠናከርና አገልግሎት ሰጪና አምራች ድርጅቶች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እንዲሳተፉ ማበረታታት፣
- ሴቶችንና የገጠሩን ነዋሪ ህዝብ የሙያ ክህሎት ባለቤት በማድረግ በራሳቸው ጉዳይ ተሰሚነታቸውን ማጠናከር፣
- ሴቶችና ልዩ ፍላጐት ያላቸው ወገኖች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እኩል የተሳትፎ እድል ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣
- በኢኮኖሚው ውስጥ በተለይም ደግሞ በታዳጊ ክልሎች የግል ስራ ፈጣሪነትን ባህል ማጠናከርና የፈጠራ ተነሳሽነትን መደገፍ፣
- ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ ዘለቄታ ያለው የፋይናንስ ስርአትና የሥራ አመራር መዋቅር መዘርጋት፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን በሚገባ ለመምራትና ለመፈፀም አስፈላጊውን የሰው ሃይል አቅም መገንባት፣

# 3. አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት መርሆዎች

3.0.1 ከላይ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ለማሳካት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ የሚመራበትና ለቀጣይ ዕድገቱ መነሻ የሚያደረጋቸው መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### የሥራ ገበያ ፍላጎት አቅጣጫን መከተል

ማንኛውም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሥራ ገበያው ለሚፈልገው ክህሎትና የብቃት ደረጃ ምላሽ የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል፡፡ ትምህርትና ሥልጠናው ብቃት ያለው የሰው ሃይል በማቅረብና ሰዎች በራስና በምንዳ ቅጥር የሚተዳደሩበትን ዕድል በማስፋት የሁሉንም የኢኮኖሚ ዘርፎች ተወዳዳሪነት ማፋጠን ይኖርበታል፡፡

### ጥራትና ተገቢነት

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ለውጥ ግብ ሁሉም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅርቦት በከፍተኛ ደረጃ ጥራቱ የተጠበቀና ተገቢነቱ የተረጋገጠ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ውጤታማ የሆነ የጥራት ማኔጅመንት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞችን ተገቢነት ይከታተላል እንዲሁም የማሠልጠኛ ተቋማት ከተቀመጠው የጥራት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ድጋፍና የምክር አገለግሎት ይሰጣል፡፡ ይህም ተግባራዊ የሚደረግበት ዋናው መሣሪያ የሙያ ደረጃ፣ የክህሎት ምዘናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓትን በመዘርጋት ነው፡፡

### እኩል የትምህርትና ሥልጠና ተሳትፎና ዕድል

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ክህሎታቸውን ለማሻሻል የሚፈልጉ ወገኖች ሁሉ እኩል ዕድል እንዲያገኙ በመደበኛ፣ መደበኛ ባልሆነና በኢ-መደበኛ (Informal) ፕሮግራሞች አማካይነት የትምህርትና ሥልጠና አቅርቦትን በማሳደግ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሳተፉ ጥረት ያደርጋል፡፡ ቀደም ሲል የነበረውን አካሄድ ማለትም አግባብነት ያለው የትምህርት ዕድል ያላገኙትን፣ ትምህርት ያቋረጡትን፣ በገጠር የሚኖሩትን፣ ልዩ የትምህርትና ሥልጠና ፍላጎት ያላቸውንና በሥራ ላይ የሚገኙ ወገኖችን የመዘንጋቱ ሁኔታ እንዲለወጥ ይደረጋል፡፡ ስለሆነም የትምህርት ደረጃ፣ የፆታ፣ የዘርና የሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ለሁሉም እንዲዳረስ ይደረጋል፡፡

**የዓምዳዊና ጐናዊ ተያያዥነት**

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የዓምዳዊና ጐናዊ ተያያዥነትን በሙያ መስኮችና በተለያዩ የብቃት ደረጃዎች መካከል እንዲሁም በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናና በአጠቃላይ ትምህርትና በከፍተኛ ትምህርት መካከል ሽግግር እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል። በመሆኑም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዜጐች በሙያ መሰላላቸው እያደጉና ያለማቋረጥ ትምህርት እየቀሰሙ እንዲሄዱ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይኖርበታል፡፡

**ተለማጭነት** (Flexibility)

በየጊዜው ለሚለዋወጠው የሥራ ሁኔታ ምላሽ ለመስጠትና በዘርፉ ያሉትን ወገኖች የሥልጠና ፍላጎት ለሟሟላት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ ሁለገብና ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህም የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሙን አደረጃጀትና ሰዎች ሙያቸውን ለማሳደግ ከሚፈልጉበት አቅጣጫ አንጻር ታይቶ ተግባራዊ የሚደረግ ነው፡፡

**የዕድሜ ልክ ትምህርት** (Life-long Learning)

የሰራተኛ ኃይል በየጊዜው እያደገ ከሚሄደው ቴክኖሎጂና የሥራ አደረጃጀት ጋር በሚጣጣም መንገድ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በሁሉም ደረጃ ለሚገኙት ባለሙያዎች በየጊዜው የሚከሰተውን አዳዲስ እውቀት የሚቀስሙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡ ይህም ሰዎች በየጊዜው ያላቸውን ክህሎት እያሻሻሉ መሄድ እንዳለባቸው የሚጠቁም ነው፡፡

**የሥርዓተ ፆታ ጉዳዮችን ያገናዘበ መሆን**

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሥርዓተ ፆታ ጉዳዮችን ያገናዘበ ይሆናል፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ለሴቶች እኩል የሥልጠና ዕድል የሚፈጥር ይሆናል፡፡ በትምህርትና ሥልጠናው ፕሮግራም ሂደት በሴቶች ላይ አድልዎ እንዳይደርስ ለማረጋገጥ፣ በሴት መምህራንም ሆነ በሰልጣኞች ላይ የወሲብ ትንኮሳ እንዳይከሰት በብቃት ለመከላከል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሥርዓተ ፆታ ሥልት እንዲነድፉ ይደረጋል፡፡

**ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከሉ አስተዋጽኦ ማድረግ**

በሁሉም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ስለ ኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ ግንዛቤ በመፍጠርና በመከላከያ መንገዶች ላይ ስልጠና በማመቻቸት ትምህርትና ሥልጠናው የበሽታውን ሥርጭት በመግታት በኩል የራሱን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት

ይደረጋል፡፡ከዚህም በተጨማሪ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ መምህራንና ተማሪዎች መገለልና አድልዎ እንዳይደርስባቸው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ፖሊሲ እንዲቀርጹ ይደረጋል፡፡

**ለአካባቢ ጥበቃ አስተዋጽዎ ማድረግ**

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በኢትዮጵያ ስለአካባቢ ጥበቃ ግንዛቤ በመፍጠር ኢትዮጵያውያን ያለውን ውሱን የተፈጥሮ ሀብት እንዲንከባከቡና በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲያውሉ በማስተማር አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

# 4. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ፅንሰሐሳባዊ መርሆዎች

## 4.1 የቴ/ሙ/ት/ሥ ተቋማት የቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ማዕከላት እንዲሆኑ ማድረግ

4.1.1 ተቋማት በዋናነት አዳዲስና ምርጥ ቴክኖሎጂዎችን በመቅዳትና ወደ ኢንዱስትሪው በማስተላለፍ ኢንዱስትሪውን በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነቱን ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቴክኖሎጂዎቹም የአካባቢን ችግሮች ለመፍታት በሚያስችሉ የፈጠራ አቅም ግንባታ ላይ ያተኮሩ እንዲሆኑና በውጤታቸውም ለሃገር ኢኮኖሚ ዕድገት ጉልህ አስተዋጽዎ እንዲያደርጉ ይፈለጋል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የሚያልፉት ሰልጣኞችም የላቀና አለም አቀፍ የስራ ሃይል ባህሪያትን የተላበሱ ስለሚሆኑ ጥቅሙን የጎላ ያደርገዋል፡፡

4.1.2 ቴክኖሎጂን የመቅዳት ተግባር በቅድሚያ ሥርዓተ ትምህርቱን በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ካለው የሙያ ደረጃ እንዲመነጭ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ በዚህ መልክ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርትን በብቃት ለማስተማር እንዲችሉ የመምህራን የክህሎት ክፍተት ከውጭ በሚመጡ አሠልጣኞች አማካይነት እንዲቀረፍ ይደረጋል፡፡ ይህ ሲሆን መምህራን ራሳቸው ለተፈላጊው ክህሎት በቅተው ሠልጣኙም እንዲበቃ በማድረግ ምርጡን ቴክኖሎጂ ወደ ኢንዱስትሪው የሚያስተላልፍ ኃይል ይፈጥራሉ፡፡

4.1.3 በተቋማቱ የሚገነባውን የምርጥ ቴክኖሎጂ አቅም በመጠቀም ኢንዱስትሪው ቀልጣፋ የአመራረት ሥርዓት እንዲይዝ በማስቻል ተወዳዳሪነትን ማጎልበት ሌላው ከተቋማት የሚጠበቅ ተግባር ሲሆን ይህንንም ምርጥ ቴክኖሎጂ በየጊዜው በአዲሱ በመተካት በተከታታይ ለገበያው ማቅረብ ይገባል፡፡ ተቋማቱ ያላቸውንም ሀብት በመጠቀም

አገልግሎት መሸጥ ሌላው ተግባራቸው ሲሆን ከዚህ የሚገኘው ገቢም የተቋማትን ብቃት የሚያሳድግ አቅም ለመፍጠር ያስችላል፡፡

4.1.4 ከዚህም በተጨማሪ ተቋማቱ በከተማና ከተማ ቀመስ አካባቢዎች የሚካሄዱትን ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራ ዘርፎች ምርታማነታቸውን እንዲያሳድጉ፣ የምርትና የአገልግሎት ጥራታቸውን እንዲያሻሽሉ ማድረግና አዳዲስ የንግድ ሥራ ጅምሮች እንዲጐለብቱ ሥልጠና በመሥጠት የቴክኖሎጂ ሽግግሩን በሚገባ ማከናወን ይገባቸዋል፡፡

## 4.2 የተቀናጀና የተዋሃደ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ዝርጋታን ኢላማ ማድረግ

4.2.1 ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መለያ በተበጣጠሰና ቅንጅት በሌለው የትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ መከናወኑ ነበር፡፡ የመደበኛው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን የመጀመሪያ እርከን ባጠናቀቁ ተማሪዎች ላይ ብቻ አተኩሮ ቆይቷል፡፡ መደበኛ ያልሆነው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ለተመረጡ ሌሎች ቡድኖች ስለሚሰጥ ክህሎታቸውን ለማሻሻል ለሚፈልጉ ሌሎች ወገኖች ሁሉ የዕድሉ ተጠቃሚ አያደርግም ነበር፡፡ በመደበኛውም ሆነ መደበኛ ባልሆነው ፕሮግራም ሠልጥነው የሚወጡት ብቃትን መሠረት አድርጐ በሚሰጠውና በኢንዱስትሪው እውቅና ባለው የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት የሚከናወን አልነበረም፡፡ በመንግስትና በግል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅርቦትም ቅንጅት አልነበረም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በገጠር አካባቢ ላሉት ሠልጣኞች ከግብርናና ግብርና ነክ ካልሆኑ ሙያዎች ጎን ለጎን የሚሰጠው ሥልጠናም በጋራ በተነደፈና በተቀናጀ ዕቅድ አይመራም ነበር፡፡ ይህም ሁኔታ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናው ተመሳሳይ ፕሮግራሞች በተለያዩ አካላት እንዲካሄዱና የሃብት ብክነት እንዲከሰት እንዲሁም፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅርቦትና ጥራት ግልጽነት እንዲጎድለው አድርጎታል፡፡

4.2.2 እነዚህን ቀልጣፋና ውጤታማ ያለመሆን ችግሮች ለመቅረፍ በቀጣይነት የሚኖረው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በሁሉም ዘርፎች የሚኖረውን የሥራ ገበያና ሙያዊ ፍላጎት የሚያስተናግድ፣ ክህሎታቸውን ለማሻሻል የሚፈልጉትን ሁሉ የሚያሳትፍና በአገሪቷ የሚሰጡትን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናዎች በሙሉ የሚያካትትና የሚያስተባብር ይሆናል። በመሆኑም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጠቅለል ባለ ሁኔታ ከከፍተኛ ትምህርት በታች በሁሉም የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና

ኩባንያዎች በመደበኛ፣ መደበኛ ባልሆነና በኢ-መደበኛ ፕሮግራሞች የሚገኘውን ትምህርትና ሥልጠና የሚገልጽ ቃል ይሆናል፡፡

4.2.3 ከላይ የተጠቀሱትን መነሻ ታሳቢዎች መሠረት በማድረግ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት በሁሉም ዘርፎች የሥራ ገበያው የሚፈልገውን ብቃት ያለውና ሁለገብ የሠራተኛ ኃይል የማፍራት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡ በተለይም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቀጥሎ ለተጠቀሱት የሰው ኃይል ገበያ ፍላጎቶች የሰለጠኑ ባለሙያዎችን የሚያቀርብ ይሆናል፡፡

- የገጠር የሥራ ገበያ፡- ይህ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በሚኖርበት የገጠር አካባቢ በግብርናና ከግብርና ውጪ በሆኑ ሥራዎች መተዳደሪያ የሚፈጥር ነው። የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በገጠር ለተሻሻለ የግብርና አመራረትና ከግብርና ውጪ ለሆኑና ጥቅም ላይ ያልዋሉ የሥራ ዕድሎችን ለመጠቀም የሚያስፈልገውን የሙያ ክህሎት የሚያስጨብጥ ይሆናል፡፡
- በከተማና ከተማ ቀመስ አካባቢዎች የሚያካሄዱ ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራ ዘርፎች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ትኩረት መካከለኛና አነስተኛ ንግድ ሥራ ድርጅቶች ምርታማነታቸውን እንዲያሳድጉ፣ የምርትና የአገልግሎት ጥራታቸውን እንዲያሻሽሉ ማድረግና አዳዲስ የንግድ ሥራ ጅምሮች እንዲጐለብቱ ሥልጠና በመሥጠት የቴክኖሎጂ ሽግግር ማእከል በመሆን ማገዝ ነው፡፡
- በዋነኛነት በከተማ የሚገኙ መንግስታዊና የግል የንግድ ስራ ድርጅቶች፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርተና ሥልጠና አሁን ላሉት ኩባንያዎች የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ሃይል ፍላጎት ለማሟላትና አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን ለመሳብ እንዲቻል በቂ የሙያተኛ ኃይል ያቀርባል፡፡
- የሲቪል ሰርቪሱ ዘርፍ የሚያቀርበውን የአገልገሎት ጥራት ለማሻሻል ከፍተኛ ፍላጎት ያለው በመሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ለዘርፉ ትኩረት ይሰጣል፡፡

4.2.4 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ ከቀድሞ በበለጠ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሥልጠና ዕድል በስፋት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ትምህርት አጠናቅቀው ከሚወጡት ሠልጣኞች በተጨማሪ የሚከተሉት ወገኖች የዕድሉ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

- ትምህርት አቋርጠው የሚወጡ፣
- ማንበብና መጻፍ የማይችሉትን ጨምሮ መደበኛ ትምህርት የሌላቸው፣

- ክህሎታቸውን ለማሻሻልና እውቅና ያለው ሙያ ለማግኘት የሚፈልጉ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ የንግድ ሥራ ድርጅቶች ባለቤቶችና ሠራተኞች (መደበኛና መደበኛ ያልሆነ የሥራ ላይ ልምምድን ጨምሮ)፣
- አርሶ አደሮችና ቤተሰቦቻቸው፣
- መሠረታዊ የክህሎት ሥልጠና ወይም ወደ ሥራ ገበያው ለመግባት ድጋሚ ሥልጠና የሚፈልጉ ሥራ አጦች፣ እና
- በኢኮኖሚው ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ ለማድረግ ልዩ ችግር ያለባቸው ዜጎች ለምሳሌ ትዳር የሌላቸው የህፃናት እናቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ተረስተው የቀዩ ብሔር ብሔረሰቦችና ሌሎች በሥራ ገበያው መገለል የደረሰባቸው ወገኖች፣

4.2.5 በማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ጉዳዮች የሴቶችን የመወሰን አቅም ለማሳደግ በሁሉም ክልሎች እንዲሁም በማንኛውም የትምህርትና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶችና አዋቂ ሴቶች የሙያ ክህሎቶቻቸውንና ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡

4.2.6 የተለያዩ ቡድኖችን ዝንባሌ፣ የክህሎትና ትምህርት ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደሁኔታው የተለያየ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን በመስጠት እንዲስተናገዱ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስርአቱ አደረጃጀትና ፕሮግራም ተለማጭ ሆኖ አዳዲስ የትምህርትና ስልጠና አሰጣጥ ዘዴዎች በየጊዜው እንዲወጡና እንዲዳብሩ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ብቃትን መሠረት ያደረገ የቴ/ሙ/ት/ሥ ሥርዓት አደረጃጀት ተግባራዊ በማድረግ፣ በሃብት አመዳደብ፣ ድጋፍ በመስጠት፣ የማሰልጠኛ ሞዱሎችን በማዘጋጀት፣ የክህሎት ምዘናና እውቅና አሰጣጥ በመሳሰሉት መንገዶች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ መደበኛ፣ መደበኛ ያልሆኑና ኢ-መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናዎች ተቀናጅተው እኩል ትኩረትና እውቅና እንዲያገኙና እንዲያድጉ ይደረጋል፡፡ ይህም ማለት ስርዓቱ በተለያዩ መንገዶች የሚሰጡ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ በትምህርት ቤትና በትብብር የሚሰጡ ሥልጠናዎች፣ የተለያዩ አጫጭር የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናዎች፣ በኩባንያዎች ውስጥ የሚሰጡ የሙያ ማሻሻያዎች፣ በተለምዶ በባለሙያዎች ለሚሰጡ የስራ ላይ ሥልጠናዎች፣ በግል ተነሳሽነት ለሚከናወኑ ራስን የማብቃት ጥረቶች ድጋፍ ይሰጣል፡፡

4.2.7 ይህም ማለት የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኃላፊዎች ትብብርና ድጋፍ የሚያደርጉት ለመደበኛ የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ብቻ አይደለም፡፡ መንግስታዊ፤ መንግሰታዊ ያልሆኑ፤ የግል ተቋማትንና ሌሎች የሙያ ትምህርት ሥልጠና

የሚሰጡትን ማጠናከር ይጠበቅባቸዋል፡፡ በኩባንያዎች በኩልና በራሳቸው የሚሰጡ የውስጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናዎችን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ልዩ ትኩረት ይሠጣል፡፡ ለዚህም ሲባል የሥራ ተለማማጆችን ተቀብለው ለሚያሰለጥኑ የማበረታቻ ሥልት ይቀየሳል፣ በመካከለኛና አነስተኛ የንግድ ሥራ ዘርፎች የሙያ ሥልጠና የሚሰጡትን ለመደገፍ ልዩ ፕሮግራሞች ይነደፋሉ፡፡

## 4.3 የባለድርሻዎች ተሳትፎ

4.3.1 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በተለያዩ ዘርፎች በተለይም በትምህርት ዘርፍ፣ በሥራ ገበያ፣ በኢንዱስትሪ፣ በጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራ፣ በግብርና፣ በገጠር ልማትና በሕዝብ አስተዳደር በቅንጅት ይከናወናል፡፡ በጥራት እነዚህን ዘርፎች እንዲያግዝና ፍላጎታቸውን እንዲያሟላ ከተፈለገ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ባለድርሻዎች በክትትልና በመፈፀም በስፋት ማሳተፍ አስፈላጊ ነው፡፡ የየራሳቸውን ሙያ፣ ልምድና ችሎታ ይዘው በጋራ አስተዋጽኦ ስለሚያደርጉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥርዓት አግባብነትና ውጤታማነት ይጎለብታል፡፡

4.3.2 በተለይ ባለድርሻዎች ቀጥሎ በተዘረዘሩት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተግባራት ውስጥ ዋናውን ሚና ሊጫወቱ ይገባል፡፡

- በፖሊሲ አወጣጥ፣ ማለትም አግባብነት ባላቸው አካላት ውስጥና መድረኮች በመሳተፍ በፖሊሲ ቀረጻና ግምገማ፣
- በፋይናንስ ማለትም ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ አስፈላጊውን ሪሶርስ በማመንጨት፣
- ጥራትን በማረጋገጥ ማለትም በሙያ ደረጃ ዝግጅትና የሙያ ምዘና በመስጠት፣
- በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማለትም ለራሳቸው ሰራተኞች ስልጠና በመስጠት፣ የሥራ ላይ ልምምድ ዕድል በመሥጠትና የትብብር ሥልጠና በማካሄድ፣
- በክትትልና ግምገማ ሥራ፣ ማለትም በፌዴራልና በክልል ደረጃዎች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስል ውስጥ በመሳተፍ በተቋማቱ ማኔጅመንት ቦርድ ውስጥ ቁልፍ ሚና በመጫወት፣

4.3.3 የአገሪቱ ኢኮኖሚና ህብረተሰቡ እያደገ በሄደ ቁጥርና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን አስመልክቶ የሚኖረው ፍላጎት እየተለወጠ ሲሄድ የተለያዩ ባለድርሻዎች አስፈላጊነትም በሂደት እየተለወጠ ይሄዳል፡፡ በአሁኑ ሁኔታ ግን በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የግልና የመንግስት ቀጣሪዎች፣ በንግድ

ምክር ቤት የሚወከሉ የንግዱ ዘርፍ አባላት የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ስራ ዘርፍ ተወካዮች (በንግድ ሥራ ማህበራቸው አማካይነት) ሠራተኞችና ተቀጣሪዎች (በሠራተኛና ሙያ ማህበራት አማካይነት) የግልና የመንግሥት ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ሰጪዎች፣ ሲቪሉ ህብረተሰብና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በገጠር አካባቢ የሚኖሩና የሚሰሩ ሰዎች (በማህበራቸው አማካይነት) ሠልጣኞችና ቤተሰቦቻቸው እንደትምህርት፣ አቅም ግንባታ፣ ግብርናና ገጠር ልማት፣ ንግድና ኢንዱስትሪ፣ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ፣ ጤና፣ ወጣቶችና ስፖርት ፋይናንስና ኢኮኖሚ በመሳሰሉና ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጋር ተዛማጅነት ያላቸው መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች ባለሥልጣናት የካውንስሉ አባላት ይሆናሉ፡፡ እነዚህ ባለድርሻዎች በተለያዩ የቴ/ሙ/ት/ሥ ተቋማት ዋንኛ ሥራዎች ውስጥ የሚጫወቱት ሚና ሊለያይ የሚችል ሲሆን የተሳትፎአቸው ዓይነትም በሚመሠረተው የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ሥርዓትና ጊዜ ይወሰናል።

4.3.4 የባለድርሻዎች ተሳትፎ ያለወጪ የሚሆን አይደለም፡፡ በመሆኑም ቀደም ሲል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አገልግሎት ተጠቃሚ ብቻ የነበሩት አሁን ጊዜያቸውን፣ ሀሳባቸውንና ገንዘባቸውን በማውጣት ለአገሪቱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መሻሻል አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ መንግሥት በበኩሉ የባለድርሻዎችን አስተዋጽኦ ለማበረታታት የተለያዩ ወገኖችን ሃሳብና ፍላጎት ለማስተናገድና ሊተገብሩት በሚችሉት መጠን ሃላፊነቱን የማጋራት ሥልት ይቀየሳል፡፡

## 4.4 የግሉ ዘርፍና የመንግሥት ሽርክና

4.4.1 የዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት ውጤታማ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቶች የተገነቡት በመንግሥታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ዘርፎች መካከል በሚኖረው ጠንካራና ግልጽ ሽርክና ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ዘርፎች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ውስጥ ይሳተፋሉ፡፡ እያንዳንዱ አካል የሚኖረውን ሚና ግልጽ በማድረግ ይህ ሽርክና ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

4.4.2 በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የመንግሥት ቁልፍ ሚና አዋጆችንና ደንቦችን በማውጣት ሥርዓቱን መቆጣጠርና ለአፈጻጸማቸው ምቹ ሁኔታን መፍጠር ነው፡፡ በዚህ መልኩ የመንግሥት ኃላፊነት ህጎችና ፖሊሲዎችን ማውጣት፣ የጥራት ማኔጅመንት ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ ማለትም የሙያ ደረጃ ምደባ ሥርዓትን የክህሎት ምዘናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓትን መቆጣጠርና መተግበር፣ የትምህርትና ሥልጠና ማዕቀፎችን መወሰን፣ እንደአስፈላጊነቱ የቴክኒክና ሙያ

ትምህርትና ሥልጠና ፋይናንስ ደንቦችን ማውጣት፣ የተቋማትን የእውቅና አሰጣጥ ሥርዓት ማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም የጥናት፣ የምርምርና ክትትል ሥራዎችን ማከናወን ይሆናል፡፡ ባለድርሻዎችን የሚያሳትፍ የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓትን ለመዘርጋት በተቀመጠው መርህ መሠረት የፌዴራል፣ የክልልና የአካባቢ የመንግስት ኃላፊዎች ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት ለመፈፀም የመሪነት ሚና በመጫወት ባለድርሻዎችን በማሳተፍ በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ ሽርክና ይፈጠራል፡፡

4.4.3 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅርቦትን በተመለከተ የግሉ ዘርፍ ወሳኝ ሚና ሊጫወት ይገባል፡፡ እስካሁን ድረስም ቢሆን የግሉ ዘርፍ በኩባንያ የውስጥ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞችና በተለይም በስፋት በተለመደው በጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራ ድርጅቶች ውስጥ በሚሰጡ የሥራ ላይ ሥልጠናዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያበረክት ቆይቷል። ሆኖም ግን የእነዚህ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናዎች ጥራት ዝቅተኛ በመሆኑ ትኩረትንና ድጋፍን ይሻል፡፡ በቀጣሪ ድርጅቶች አማካይነት ከሚቀርቡት የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናዎች በተጨማሪ የግል ተቋማት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅርቦት ውስጥ ያላቸው ድርሻ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሄድ ላይ ነው፡፡

4.4.4 የግል የቴክኒክና ሙያ ትምርትና ሥልጠና በብዙ መልኩ ጠቃሚ ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በግሉ ዘርፍ ያለውን ልምድና አቅም አሟጦ በመጠቀም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥራትና ተገቢነትን ለማሻሻል ይረዳል፡፡ ሁለተኛ በዘርፉ ኢንቨስት የሚደረገውን ሀብት በማሳደግ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅርቦት ጨምሮ የዜጎችን የመሳተፍ ዕድል ያሰፋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን በማዳረስ ረገድ በመንግስት ላይ የሚኖረውን ጫና በመቀነስ መንግስት ፖሊሲ በማውጣትና ድጋፍ በመስጠት ተግባሮች ላይ እንዲያተኩር ያግዘዋል፡፡በመሆኑም የግል የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ሰጪዎች የበለጠ ሊጠናከሩ ይገባል፡፡ የግል ሥልጠና ሰጪዎች ጐራ የሚያጠቃልለው የንግድና የንግድ ያልሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን፣ የኩባንያ ውስጥ ሥልጠና የሚሰጡ የግል ኩባንያዎችን፣ ለራስ ድርጅት ሠራተኞች የሚሰጡ ሥልጠናዎችን፣ የሥራ ላይ ልምምድና የትብብር ሥልጠና የሚሰጡ ድርጅቶችንና፣ በጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰጡ ሥልጠናዎችንና በተለይም ባህላዊ የሥራ ላይ ልምምዶችን ነው፡፡

4.4.5 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የበላይ አካላት ከባለድርሻዎች ጋር በመሆን የግል የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና አቅርቦት እንዲያድግ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ፡፡ ይህም በፍቃድና እውቅና በመሰጠት የሚያበረታታ የቁጥጥር ሥርዓት መፍጠርንና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የሚሰጠውን የድጋፍ አገልግሎት በሙሉ የሚያገኙባቸውን ሁኔታዎች ማመቻቸትን ያጠቃልላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አካላት ከግብርና ከቀረጥ ክፍያ ነፃ የማድረግና የመሳሰለውን በማጤን እንደሁኔታው የፋይናንስ ማበረታቻ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋሉ።

4.4.6 አሁን ባለው ሁኔታ ግን የግሉ ዘርፍና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አቅም ደካማ መሆኑን ከግምት በማስገባት በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና አቅርቦት መንግስት ዋናውን ሚና መጫወቱን ለተወሰነ ጊዜ ይቀጥላል፡፡ ይህም በሚሆንበት ጊዜ በአብዛኛው የሚያተኩረው በአሁኑ ወቅት የግሉ ዘርፍ በማይገባባቸውና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግቦችን በማሳካት በኩል ስትራቴጅካዊ ጠቀሜታ ባላቸው የሙያ መስኮች ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ለረጅም ጊዜ የሚሰጡ አዲስ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናዎችን፣ ልዩ ክህሎት የሚጠይቁ የቴክኖሎጂ ሥልጠናዎችን፣ ራቅ ባሉ አካባቢዎች የሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናዎችንና የመሳሰሉትን የመንግስት ተቋማት ዋና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅራቢ ሆነው ይቀጥላሉ፡፡

4.4.7 በአገሪቷ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሌላው የመንግሥት ቁልፍ ሚና የግልና የመንግሥት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪ ተቋማትን አቅም ለመገንባት ድጋፍ የሚሰጥበትን መንገድ መቀየስ ነው፡፡ ይህም ለቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና መምህራንን ማሰልጠንና ሌሎች የተቋማቱን አቅም ለመገንባት የሚረዱ ድጋፎችን መስጠትን ያጠቃልላል፡፡

## 4.5 ውጤትን መሠረት (Outcome-based) ያደረገ ሥልጠና

4.5.1 በስትራተጂው ራዕይና ዓላማ ውስጥ እንደተገለጸው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ግብ ሥርዓቱ ለአገሪቷ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ኑሮ ዕድገት የጀርባ አጥንት የሚሆኑ ብቃትና ችሎታ ያላቸው ሁለገብ ባለሙያዎችን ማፍራትና በርካታ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ የአገሪቷ ኢኮኖሚ ዘርፎች ተቀጥረው መሥራት እንዲችሉና የግል ሥራ እንዲፈጥሩ ማድረግ ነው፡፡

4.5.2 ይህንን ግብ ከዳር ለማድረስ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዳሉት ዘመናዊ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ሥርዓቶች ሁሉ የአገሪቱ የቴክኒክና ሙያ ትምህትና ሥልጠና ሥርዓት ውጤትን መሠረት ባደረገ መልኩ እንደገና መደራጀት ይኖርበታል፡፡ ይህም ማለት በሥራ ገበያው ውስጥ የሚፈለገው ብቃት የትምህርቱና ሥልጠናው ማነፃፀሪያ ሆኖ የሚያገለግልና ሁሉም ተቋማት የቴክኒክና ሙያ ትምህትና ሥልጠና ህግና ደንቦች ዜጎችን ብቁ ለማድረግ በሚያግዝ መልኩ የሚቀረፁ ይሆናሉ፡፡

4.5.3 ብቃት (Competence) ሰፊ ንድፈ ሃሳብ ሲሆን በሥራ ገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት ምርታማና ሁለገብ ኢንተርፕሪነየር እንዲሁም ተቀጣሪ ወይም ሠራተኛ ለመሆን ብሎም የራስን ኢኮኖሚያዊ አቅምና ማህበራዊ ኑሮ ለማሳደግ አስፈላጊ የሆነውን ክህሎት፣ እውቀት፣ ዝንባሌ የሚያጠቃልል ነው፡፡

4.5.4 ብቃት የሚገለጸው በሥራው አለም እውቀትና ልምድ ባላቸው ሰዎች በሚዘጋጅ የሙያ ደረጃ ነው፡፡ የሙያ ደረጃ የሁሉንም ትምህርትና ሥልጠና ውጤት የሚተረጉመው ከሥራው ገበያ ፍላጎት አንፃር ሲሆን ይህም በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ውስጥ ለሚደረጉ የጥራት ማኔጅመንት ሥራዎች በሙሉ እንደ ማነፃፀሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡

4.5.5 የቴክኒክና ሙያ ትምህትና ሥልጠና አሰጣጥ ጥራት የሚመዘነው ሠልጣኙ ያገኘውን ብቃት በሚያረጋግጥ የሥራ ሂደት ነው፡፡ ይህም ተግባራዊ የሚደረገው የሙያ ደረጃዎችን መሠረት አድርጎ በሚከናወነው የሙያ ብቃት ምዘና ነው፡፡ ምዘናውን ያለፈ ሠልጣኝ (አንድ ምዘና ወይም ተከታታይ ምዘናዎች ሊደረጉ ይችላሉ) ብሔራዊ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኛል፡፡ ይህም ሠልጣኙ በሠለጠነበት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መስክ ብቁ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የሙያ ምዘናና የብቃት ማረጋገጫ ምሥክር ወረቀት በማንኛውም መደበኛ፣ መደበኛ ያልሆነና በኢ-መደበኛ ትምህርትና ሥልጠና ተፈላጊውን ብቃት ላገኘ ሁሉ ክፍት ይሆናል፡፡ ስለሆነም ውጤትን መሠረት ያደረገ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ለመደበኛ፣ መደበኛ ላልሆነና ለኢ-መደበኛ ሥልጠናዎች እኩል ዋጋ በመስጠት በኩል እንደዋና መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡

4.5.6 ብቃትን መሠረት ባደረገ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ውስጥ የትምህርትና ሥልጠና ስጪዎች ግብ ሰልጣኞች በተቀመጠው የሙያ ብቃት ደረጃ መሠረት ተግባራቸውን ማከናወን ችለው የምስክር ወረቀት ለማግኘት እንዲችሉ

ተፈላጊውን ክህሎት፣ እውቀትና ዝንባሌ ማስጨበጥ ነው፡፡ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪ ተቋማት በአገር አቀፍ የሙያ ደረጃ ላይ የተመሠረተና የመማር ሂደቱን የሚያፋጥን ሥርዓተ ትምህርት መቅረጽ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሥርዓተ ትምህርቱም የሠልጣኞቹንና የሥራ ገበያን ልዩ ፍላጎት ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፡፡ ብቃትን መሠረት ያደረገ የማኔጅመንት ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሲሆን ቀደም ሲል ሥርዓተ ትምህርትን በማዕከል ቀርጾ ለሁሉም እንዲፀና አድርጐ የማስተላለፉ አሰራር እንዲቀር ያደርጋል፡፡ በምትኩ እያንዳንዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪ እንደተቋሙ ሥርዓት ለራሱ ሠልጣኞች ከፍተኛ ጥራት ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መስጠት የሚያስችል አመቺ ሥርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል፡፡

4.5.7 በአሁኑ ሁኔታ የአገሪቷ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የዕድገት ደረጃ ዝቅተኛ በመሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪዎች ተገቢውን ሥርዓተ ትምህርት ቀርጸው ጥራት ያለው ትምህርትና ሥልጠና መስጠት እስኪችሉ ድረስ በዚህ ረገድ አስፈላጊውን ድጋፍ ማግኘታቸውን ሥርዓቱ ያረጋግጣል ፡፡ ይህም ድጋፍ ሥርዓተ ትምህርት አቀራረጽ መመሪያዎችን እንዲሁም ሞዴል ሥርዓተ ትምህርቶችን አዘጋጅቶ በማቅረብና በመሳሰሉት መንገዶች ሥልጠና ሰጪዎቹን ማገዝን ያጠቃልላል፡፡

## 4.6 ያልተማከለ አሠራር

4.6.1 በአገሪቷ ያልተማከለ የአስተዳደር ፖሊሲ መሠረት የአዲሱን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት አገልግሎት ቀልጣፋና የተጠቃሚዎችን ፍላጎት የሚያሟላ ለማድረግ የተግባር ኃላፊነቶች ቀስ በቀስ ወደ ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን እንዲወርዱ ይደረጋል፡፡

4.6.2 ባልተማከለ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ ሥርዓት ውስጥ የፌዴራል መንግሥቱ ኃላፊነት አገር አቀፍ ፖሊሲ መቅረጽ፣ ህግና ደንቦችን ማውጣት ማለትም የሙያ ደረጃ፣ የክህሎት ምዘናና የምስክር ወረቀትና እውቅና አሰጣጥ፣ የመምህራን ሥልጠና ሥርዓት የመሳሰሉትን ደንቦች ማዘጋጀትና ማስተባበር፣ በተዋረድ የአስተዳደር እርከን ላይ የሚገኙትን አካላት የማማከርና አስፈላጊውን የአፈጻጸም ድጋፎችን መስጠት ይሆናል፡፡

4.6.3 የአዲሱ የቴክኒክና ሙያ ትምህትና ሥልጠና ሥርዓት የማስፈጸም ዋና ኃላፊነት የሚወድቀው በክልል መንግሥታት ላይ ሲሆን እነርሱም በተዋረድ እንደ አስፈላጊነቱ

ኃላፊነቶቻቸውን ወደ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ያወርዳሉ፡፡ የመንግስት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣናት በየክልላቸው የሚሰጠውን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ያቅዳሉ፣ ያስተባብራሉ፣ ድጋፍና ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡ እንዲሁም መንግሥታዊ ላልሆኑና የግል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪዎች ድጋፍ የሚሰጥበትን መንገድ ይቀይሳሉ፣ የፌዴራል መንግሥቱን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጄንሲን በመወከል ያሉትን ህጎችና ደንቦች ያስፈጽማሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የዞንና የወረዳ የቴክኒክና ሙያ ትምህትና ሥልጠና ጽ/ቤቶችና ካውንስሎች አቅም እንዲገነባ ያደርጋሉ፣ ባላቸው የሥልጣን ወሰን የሥልጣን ውክልና ይሰጣሉ፡፡

4.6.4 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሠጣጥ ፍላጎት ላይ የተመሠረተና ከሥራ ገበያው ጋር የተቀናጀ መሆኑን ለማረጋገጥ ዋና ዋና ኃላፊነቶችን በቀጥታ ለማስልጠኛ ተቋማት በመስጠት ላይ ትኩረት ይደረጋል፡፡ የሌሎች አገሮች ልምድ በግልፅ የሚያሳየው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በሀብት አጠቃቀም፣ በስልጠና ፕሮግራም ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃላይ ማኔጅመንት በኩል በሚሰጣቸው የአሠራር ነፃነትና በስልጠና ጥራትና ውጤት መካከል ቀጥተኛ ግኑኝነት መኖሩ ነው፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት በመካከለኛ ጊዜ ዕቅድ ለመንግስት የማሰልጠኛ ተቋማት በዕቅድ ዝግጅትና ማኔጅመንት በኩል ሰፊ ሃላፊነት የመስጠት ዓላማ አለው፡፡ ወደፊት የማሰልጠኛ ተቋማቱ ለሚሰጡት ሥልጠና ስኬት ሙሉ ሃላፊነት ይረከባሉ፡፡ እንደ ሥራ አፈጻጸማቸው ሁኔታም የፋይናንስ ድጋፍ የሚሰጥበትን መንገድ በመቀየስ ይህ አሠራር ይጠናከራል፡

4.6.5 በተቋም ደረጃ ከሚሰጠው ሰፊ የማኔጅመንት ኃላፊነት ጋር የመንግስት ማሰልጠኛ ተቋማት የአካባቢው የንግድ ህብረተሰብ ተወካዮችን ጨምሮ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የአካባቢው አካላት የተወጣጡ የማኔጅመንት ቦርድ ያቋቁማሉ፡፡ የማኔጅመንት ቦርዱም ትምህርት ቤቱን የመቆጣጠር እንዲሁም ዕቅድ፣ በጀትና ሪፖርቶችን የማጽደቅ ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡ መንግሥታዊ ያልሆኑና የግል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪዎችም ከአካባቢው የኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር ተቀናጅተው መስራት እንዲችሉ በተመሳሳይ ሁኔታ የማኔጅመንት ቦርድ እንዲያቋቋሙ ይበረታታሉ፡፡

4.6.6 ያልተማከለ አሠራርን ተግባራዊ ለማድረግ በሁሉም ደረጃ በተለይም በዞን፣ በወረዳና በተቋማት ደረጃ የአቅም ግንባታ ሥራ መጠናከር ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም በፌዴራልና በክልል ያሉት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኃላፊዎች በተዋረድ ለሚገኙ

የአስተዳደር እርከን ኃላፊዎች ፣ ለተቋማቱ የቦርድና የማኔጅመንት አባላት ሥልጠናና አቅም ግንባታ የሚውል በቂ ሪሶርስ ይመድባሉ፡፡

## 4.7 ቀልጣፋ አሠራር (Efficiency) በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና

4.7.1 ያለውን ውስን ሪሶርስ በአግባቡ ለመጠቀም እንዲቻል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓትን ቀልጣፋ በማድረጉ በኩል ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡ ይህም በሁሉም ደረጃ የሚኖረውን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማኔጅመንት፣ ሥልጠናው የሚሰጥበትን ዘዴና ሠልጣኙ ቀደም ሲል የተማረውን ትምህርት ውጤት ዕውቅና የመስጠት አግራጭን ያካትታል፡፡

4.7.2 ተገቢ ተቋማዊና የሰው ኃይል ልማት ፖሊሲዎችን በመቅረጽ፣ ኃላፊነትንና ተግባራትን በግልጽ ለይቶ በማስቀመጥ በሁሉም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ደረጃዎች ቅልጥፍናን ማሳደግ ይቻላል። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የአቅም አጠቃቀምን በማሳደግ፣ የሰው ኃይልና ፋይናንስ ማኔጅመንትን በማሻሻልና የሥልጠና መሣሪያዎችንና ቁሳቁስን በተሻለ ሁኔታ ሥራ ላይ በማዋል የሥልጠና ተቋማትን ውስጣዊ የአሠራር ቅልጥፍና በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻል ይቻላል፡፡ በመሆኑም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ማኔጅመንት ችግሮችና ፍላጎት በጥልቀት ከተመረመረ በኋላ የማኔጅመንት አቅም ግንባታ ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ በሂደት ለተቋማቱ የሚሰጠውን የማኔጅመንት ኃላፊነት ውክልና የተቋማቱን የውስጥ አሰራር ቅልጥፍናን እንደሚያሻሽል ይጠበቃል፡፡ ይህ አካሄድ በመንግስት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሥራ አፈጻጸምን መሠረት ያደረገ የበጀት አመዳደብ ሥርዓትን ተግባራዊ በማድረግ ይታገዛል።

4.7.3 ወጪ ቆጣቢ በሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ ሥልቶች ላይ ትኩረት ማድረግ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓትን ቅልጥፍና ለማሳደግ የሚያስችል ሌላ ጠቀሚ አካሄድ ነው፡፡ በመሆኑም በማሠልጠኛ ተቋማትና በድርጅቶች/ በኩባንያዎች ትብብር የሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡ የሥልጠና ተቋማቱም ወጪ ቆጣቢ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችሏቸውን የተለያዩና የተሻሉ ዘዴዎች እንዲቀይሱ ይበረታታሉ፡፡

4.7.4 ቀደም ሲል ሠልጣኙ መደበኛ ባልሆነና በኢ-መደበኛ ላገኘው የቴክኒክና ሙያ እውቀት እውቅና በመስጠት ከመደበኛው ትምህርትና ሥልጠና ጋር ማቀናጀት አላስፈላጊ

ሥልጠናንና የትምህርት ድግግሞሽን ስለሚያስቀር ለአሠራር ቅልጥፍና መስፈን ከፍተኛ አስተዋጾ ይኖረዋል፡፡ ይህም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን በሞዱዩል በማዘጋጀት፣ መደበኛ ፣ መደበኛ ባልሆነና በኢ-መደበኛ ለተገኘው ክህሎት መሠረታዊ አቅጣጫ የሚያሳይ የሙያ ደረጃን በማዘጋጀትና የሙያ ምዘናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥን ለሁሉም ዓይነት ሥልጠናዎች ክፍት በማድረግ የሚተገበር ይሆናል፡፡

# 5. ውጤትን መሠረት ላደረገ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማዊ ብቃትን ማሳደግ

5.0.1 ቀደም ሲል የነበረው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ ከሙያ ደረጃ ባለመነሳቱ የሥራ ገበያ ፍላጎት ለማርካት አልቻለም፡፡ በመሆኑም በአገሪቷ የሚሰጠውን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥራትና ተገቢነት ለማሳደግ ውጤትን መሠረት ያደረገ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት መገንባት የማሻሻያው የትኩረት ማዕከል ሊሆን ይገባል፡፡ ውጤትን መሠረት ያደረገ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት በአገሪቷ በስፋት መተግበር መደበኛ ባልሆነና በኢ-መደበኛ ስልት ለሚሰጡ ትምህርትና ሥልጠናዎች ተገቢውን እውቅና ስለሚሰጥ ቀደም ሲል ተረስተው ለነበሩ ሙያተኞች ሙያቸውን እንዲያሳድጉ በር ይከፍትላቸዋል፡፡


5.0.2 ውጤትን መሠረት ባደረገው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የፌዴራል መንግስት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥራትንና ተገቢነትን የማረጋገጥ ኃላፊነቱን፦

- ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ደረጃ ማነፃፀሪያ ሆኖ የሚያገለግል ከአለም አቀፍ ደረጃ ጋር የሚመጣጠን አገር አቀፍ የሙያ ደረጃን በማውጣት ፣
- የሙያ ምዘናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓትን በማደራጀት በተመደበው የሙያ ደረጃ መሠረት ምዘናውን ላለፉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጥ በማድረግ ይወጣል፡፡

5.0.3 ውጤትን መሠረት ያደረገ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓትን በመዘርጋት ሂደት ውስጥ መንግስት ሕጎችንና ደንቦችን የማውጣት ሃላፊነት ሲኖረው ይህን የሚያደርገው ከአሠሪዎችና ስለ ሥራ ገበያው ፍላጎት እውቀት ካላቸው ባለሙያዎች ጋር በመተባበር ይሆናል፡፡

## ውጤትን መሰረት ያደረገ የቴ/ሙ/ት/ሥ ሥርዐት አደረጃጀት

የ ጥ ራ ት ማ ኔ ጅ መ ን ት



## 5.1 የሙያ ደረጃ ምደባ ዝግጅት

5.1.1 የሙያ ደረጃ ሠራተኛው ከሥራ ገበያ ፍላጎት አንፃር ሊኖረው የሚገባውን ብቃት የሚገልጽ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የሙያ ደረጃ አንድ ግለሰብ በአንድ በተወሰነ የሙያ ዘርፍ ማወቅ ያለበትን የሚያመለክትና የሚጠበቅበትን የብቃት ደረጃ በአጠቃላይ የሚገለጽ ነው፡፡ ብቃት ሲባል አንድ የተወሰነ ሥራን ለማከናወን የሚያስፈልግ ክህሎት፣ እውቀትና ዝንባሌን ያጠቃልላል፡፡ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ለሚታቀፉ ለሁሉም የሙያ ብቃት ደረጃዎች በሁሉም የትምህርትና ስልጠና መስኮች የሙያ ደረጃ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡ እያንዳንዱ የሙያ ደረጃ  በሥራ ገበያ ውስጥ ሊያስቀጥሩ በሚችሉ የተለያዩ የብቃት ደረጃዎች ስብሰብ የሚከፋፈል ሊሆን ይችላል፡፡ የሙያ ደረጃዎቹም በአገር አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባለው ቅጽ መሠረት የሚገለፁና ህዝብ እንዲያውቃቸው የሚደረጉ ይሆናሉ፡፡ ይህም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ደረጃን አስመልክቶ ለቀጣሪዎች፣ ሰልጣኞችና ሥልጠና ሰጪዎች ግልፅ የሆነ አሠራር እንዲኖር ያደርጋል፡፡

5.1.2 የሙያ ደረጃ የሚወጣበትን ሁኔታ ማደራጀትና ማመቻቸት የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ኃላፊነት ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን የሙያ ደረጃዎች በሥራው ዓለም የሚፈለገውን ብቃት የሚያንጸባርቁ ስለሆኑ በበለጸጉና ቴክኖሎጂ አመንጪ በሆኑ ሀገሮች በሥራው ዓለም ያሉት ባለድርሻዎች በተለይም አሰሪዎች በደረጃ አወጣጡ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡  በመሆኑም ኤጄንሲው በደረጃ አወጣጡ ሂደት በሥራው ዓለም ስለሚፈለገው ክህሎት በቂ እውቀት ያላቸው ባለሙያዎችን ያሳተፈ የባለሙያዎች ቡድን ያቋቁማል።

5.1.3 ከአለም አቀፍ ደረጃ የተወሰደ የሙያ ደረጃ እንዱስትሪውን በማሳተፍ የሃገራችንን ራእይ እውን ማድረግ የሚያስችል ሆኖ መጣጣሙ ተገምግሞ ከተረጋገጠ በኋላ በፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጄንሲ ብሔራዊ አገር አቀፍ የሙያ ደረጃ ሆኖ ይጸድቃል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካሉትና ተቀባይነት ካገኙት የደረጃ አወጣጥ ዘዴዎች ውስጥ አመቺውን ለመጠቀም በመጀመሪያ ስለሚመረጠው ዘዴ የጋራ ስምምነት ሊደረስ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጄንሲ ለደረጃዎቹ አንድ አይነት ቅጽ እንዲሁም ደረጃዎች ስለሚጸድቁበትና በመጨረሻም ታትመው ስለሚወጡበት ሁኔታ የአሠራር ቅድመ ተከተል ያዘጋጃል፡፡

5.1.4 የሙያ ደረጃ አወጣጡ የሥራ ገበያ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም የሥራ ደረጃ የሚወጣላቸውን የሥራ ዘርፎች የመለየትና የማቧደኑ ሥራ የሚከናወነው አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የአገሪቱን የሥራ ገበያ ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡ ይህም የአገሪቷን የሥራ ገበያ ማጥናትን ይጠይቃል፡፡ የሥራ ገበያ ጥናት በቴክኖሎጂ ወይም በኢኮኖሚ ዕድገት ምክንያት የሚከሰተውን የተፈላጊ ብቃት ለውጥን ተከትሎ ባሉት ብሄራዊ የሙያ ደረጃዎች ላይ የሚደረገውን ማሻሻል ወይም ለውጥ ለመለየት ያስችላል፡፡

5.1.5 ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የሚወጣው የሙያ ደረጃ አገር አቀፍ የሙያ ምደባ ሥርዓት መሠረት የታወቁ የሥራ መደቦችን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ለማረጋገጥ የሙያ ደረጃ የሚወጣላቸውን የሥራ ዘርፎች የመለየትና የማቧደኑ ሥራ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሚከናወን ይሆናል፡፡

5.1.6 የኢትዮጵያ ሠራተኞች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ብቃት እንዲኖራቸው ለማድረግ የአገሪቱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የብቃት ደረጃ የዓለም አቀፍ በጠበቀ መልኩ ይቀረጻል፡፡በመሆኑም የሚወጡት የሙያ ደረጃዎች በአገሪቱ የሥራ ገበያ ፍላጎት ላይ የተመሠረቱ ሆነው በተቻለ መጠን የዓለም አቀፍ ብቃት ደረጃን የተላበሱ መሆን ይገባቸዋል፡፡ የሙያ ደረጃ አወጣጥ ሥራን ለማቀላጠፍ የሌሎች አገሮችን ደረጃ አወጣጥ ዘዴን ከአገራችን ሁኔታ ጋር በማጣጣም መጠቀም ወይም የሙያ ደረጃዎችን በቀጥታ ሥራ ላይ ማዋልን የሚያጠቃልል ይሆናል፡፡

5.1.7 የሙያ ደረጃ በአገር አቀፍ ደረጃ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ አማካይነት ተዘጋጅቶና ጸድቆ የሚወጣ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን እንደ ክልሉ ወይም የአንድ አካባቢ የሥራ ገበያ ፍላጎት በተዋረድ የአስተዳደር እርከን የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ባለስልጣናት ተገቢ የሆነውን የሙያ ደረጃ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡ በእንዲህ ዓይነት መልኩ ለሚወጣ የሙያ ደረጃ አገር አቀፍ ዕውቅና በሚሰጥበት ሁኔታ ላይ ተገቢው ደንብ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

## 5. 2 የሙያ ብቃት ምዘናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

5.2.1 ብቃትን መሠረት ባደረገ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የሙያ ብቃት ምዘና አድርጎ የምስክር ወረቀት መሰጠት የአንድን ግለሰብ የሙያ ብቃት ለማረጋገጥ የሚያስችል መሣሪያ ነው፡፡ በተለያዩ ደረጃዎች ተለይተው ለሚታወቁ

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የብቃት ደረጃዎች የሙያ ምዘና ተደርጎ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡ የሙያ ብቃት ምዘናውን ላለፉት አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

5.2.2 የሙያ ብቃትና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ በማንኛውም መልኩና በየትኛውም ቦታ ለተማሩና ለሠለጠኑ በሙያ ደረጃው የሚፈለጉ መስፈርቶችን በማሟላት ብቃት አለን ብለው ለሚቀርቡ ሁሉ ክፍት ይደረጋል፡፡ ቀደም ሲል እንደነበረው ልምድ አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ማግኘት መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራምን በመከታተል ብቻ ላይ የሚወሰን አይሆንም፡፡ ለወደፊቱ ለማንኛውም መደበኛና መደበኛ ያልሆነ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራምን ላጠናቀቁ እንዲሁም በኢ-መደበኛ ወይም ራስን በማስተማር ክህሎትን ለጨበጡ ሁሉ የሙያ ብቃት ምዘናው ክፍት ይደረጋል። በዚህም መሠረት የምስክር ወረቀት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም የተለያዩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ ሥልቶችን ለማቀናጀትና ቀደም ሲል ሰዎች ለጨበጧቸው ክህሎቶች እውቅና ለመስጠት የሙያ ብቃት ምዘና ዋና መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ይህም ህዝቡ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የሚገኘውን ብቃት በስፋት እንዲያገኝ ከፍተኛ አስተዋጽዎ ይኖረዋል፡፡

5.2.3 የሙያ ብቃት ምዘና የሚደረገው በተመረጡና እውቅና በተሰጣቸው የግልና የመንግስት የምዘና ማዕከላት ነው፡፡ ምዘናው እውቅና በተሰጣቸው ፈታኞች የሚደረግ ሲሆን እነዚህም አሰልጣኞች ወይም በሥራው ዓለም ያሉ ባለሙያዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የቴክኒክና ሙያ ሰልጣኞችን የመቀጠር እድል ለማሳደግ ትምህርትና ስልጠናው እንዲሁም የምስክር ወረቀቱ በአሰሪዎች እውቅና ሊያገኝ ይገባል፡፡ በመሆኑም የኢንዱስትሪው ባለሙያዎች ሁልጊዜ የሙያ ብቃት ምዘና ቡድኑ ቁልፍ አባላት እንዲሆኑ ያስፈልጋል። በተቻለ መጠን የንግዱ ህብረተሰብ ወይም የአሠሪዎች ማህበራት በምዘና ሥርዓቱ አመራር ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

5.2.4 አገር አቀፍ የሙያ ብቃት ምዘናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጄንሲ ኃላፊነት ይሆናል፡፡ ኤጄንሲው የሙያ ምዘና ፈተና የሚዘጋጅበትን ደንብ እና የአሠራር ቅደም ተከተል ያወጣል፣ ምዘናው እንዲካሄድ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ በሥርዓቱ ላይ ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል፡፡ የሙያ ብቃት ምዘናን ተግባራዊ ማድረግ ማለትም ምዘናው በአግባቡ ተካሄዶ

የምስክር ወረቀት መሰጠቱን ማረጋገጥ የክልል መንግስት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ባለስልጣናት ኃላፊነት ይሆናል፡፡

5.2.5 የሙያ ብቃት ምዘና አፈፃፀምን ለማመቻቸትና ምዘናውን ለማካሄድ በየክልሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የብቃት ማረጋገጫ ማዕከላት (Centers of competence) ይቋቋማሉ።የሙያ ብቃት ምዘናው በቀላሉ በማይደረስባቸው አካባቢዎች ያሉትን ጨምሮ ለሁሉም ዜጎች ክፍት እንዲሆን በተወሰኑ የሙያ መስኮች ተጨማሪ የምዘና ማዕከላት ተቋቁመው እውቅና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ይህም በተለይ የንግድ ድርጅቶችንና የተሻሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን ያጠቃልላል፡፡

5.2.6 የየክልሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኃላፊዎች የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ሲወክላቸው የሙያ ብቃት መመዘኛውን በአጥጋቢ ሁኔታ ላለፉት አገር አቀፍ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣሉ፡፡

## 5.3 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ብቃት ማዕቀፍ

5.3.1 ለብቃት የሚሰጠውን ዋጋ ለይቶ ለማስቀመጥና በተለያዩ መንገዶች የሚገኙትን ብቃቶች አቻነት ለማረጋገጥ እንዲሁም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ውስጥ ትስስር እንዲኖር ለማድረግ አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ብቃት ማዕቀፍ ይዘጋጃል፡፡ ይህም ማዕቀፍ፤

- የሚረጋገጡ የሙያ ብቃት ደረጃዎችን ለይቶ ያስቀምጣል፣
- የብቃት ደረጃ መግለጫዎችን ያወጣል ማለትም አንድን ሥራ ተረክቦ የሚሠራ ሙያተኛ ሊኖረው ስለሚገባ የብቃት ደረጃና ይዘት እንዲሁም የኃላፊነት ደረጃ ለይቶ ያስቀምጣል፣
- ከአንዱ ሙያ ወደ ሌላ፣ ከአንዱ የብቃት ደረጃ ወደ ሚቀጥለው ደረጃ የሚኖረውን ጕናዊና አምዳዊ ትስስር የሚገልጽ (ለምሳሌ ተመሳሳይ ሥልጠናዎችን በማየት) መመሪያ ያወጣል፤

5.3.2 በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሚገኘው የብቃት ማስረጃ ወደ አጠቃላይ ትምህርት ሥርዓት የሚያስገባና ወደ ከፍተኛ ትምህርት የሚያሸጋግር አማራጭም ሊሰጥ ይገባል፡፡ በመሆኑም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የብቃት ማዕቀፍ ከአገርአቀፍ የብቃት ማዕቀፍ ጋር በሚቀናጅ መልኩ የሚቀረጽ ይሆናል፡፡ አገር አቀፍ ማዕቀፉ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃን፣ እንዲሁም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናንና

ከፍተኛ ትምህርትን ጨምሮ በአጠቃላይ የአገሪቷ ትምህርትና ስልጠና ሥርዓት ውስጥ የሚገኙ የብቃት ደረጃዎችንና በተለያዩ የብቃት ደረጃዎች መካከል የሚኖረውን ግንኙነትና አቻነት ለይቶ ያስቀምጣል፡፡ ከአጠቃላይ ትምህርት ወደ ቴክኒክና ሙያ ለመዘዋወር እንዲሁም ከቴክኒክና ሙያ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመሸጋገር የሚያስችሉ መመሪያዎችና ተፈላጊ ሁኔታዎች ይወጣሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቱን የዝውውር ሁኔታ ለማመቻቸትና የሥልጠና ደረጃዎች የሚለኩበትን የጋራ መነሻ ሚዛን ለማበጀት እንዲቻል አገርአቀፍ የብቃት ማዕቀፍ ማዘጋጀት ዋና መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡

5.3.3 አገር አቀፍ የብቃት ማዕቀፍን በጋራ አዘጋጅቶ ለማዳበርና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ክህሎትና የከፍተኛ ትምህርት የብቃት ፖሊሲዎችን ለማቀናጀት እንዲቻል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኃላፊዎች አግባብነት ካላቸው የአጠቃላይ እና የከፍተኛ ትምህርት ኃላፊዎች ጋር በመቀናጀት ይሠራሉ፡፡

5.3.4 በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የተገኘውን የብቃት ደረጃ ባለው አገር አቀፍ የትምህርት ሥርዓት መሠረት ተጨማሪ የትምህርት ዝግጅት ቢጠይቅ (ወይም ከሚፈለገው በላይ ሆኖ ቢገኝ) ተገቢው የማሟያ ትምህርት የሚያገኝበት (ወይም ለተጨማሪው ትምህርት እውቅና ተሰጥቶ ሠልጣኙ ነፃ (exemption)የሚሆንበት) ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡

# 6. ተለማጭ የሆነ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ ሥርዓትን መዘርጋት

6.0.1 ውጤትን መሠረት ያደረገ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ አቅርቦቱን እንደሁኔታው ለመለወጥ ከፍተኛ አመቺነት አለው፡፡ ለወደፊቱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪዎች እንደ ሠልጣኞቻቸውና የሥራ ገበያው ፍላጎት የሚሰጡትን ትምህርትና ሥልጠና በራሳቸው የሚወስኑ ይሆናሉ፡፡ አዲሱ ሥርዓት ሠልጣኙን ማዕከል ያደረገና ሠልጣኞቹ በትምህርትና ሥልጠና ሂደት ኃላፊነት የሚረከቡበት ዘመናዊ የማስተማርና የመማር ዘዴ ሥራ ላይ እንዲውል ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ነው፡፡ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ውስጥ ብቸኛ ማነፃፀሪያ (benchmark) ተደርጎ የተቀመጠው ውጤት ሲሆን ይህም የሚገለጸው በሙያ ደረጃ ውስጥ በተቀመጡ ተፈላጊ ብቃቶች ነው፡፡

6.0.2 በዚህ ሰነድ ክፍል 7.3 በስፋት እንደተገለጸው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪዎች ሠልጣኞች ፍላጎት መሠረት ሥርዓተ ትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራም

መቅረጽ እንዲችሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አካላት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣሉ ፡፡

## 6.1 ሞዱላራዊ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥን እንደ መርህ መከተል

6.1.1 በሙያ ደረጃ የተቀመጡትን አስፈላጊ የብቃት ደረጃዎች ለማስጨበጥ የሚቀየሰውየቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም በሞዱል መልክ የሚደራጅ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ሞዱል በተናጥል ወይም በጥምርታ በሥራ ገበያ ተፈላጊ የሆነውን ብቃት ይገልፃል፡፡ እያንዳንዱ የሥልጠና ሞዱል በአጥጋቢ ሁኔታ መጠናቀቁ የሚረጋገጠው በሙያ ብቃት ደረጃ በተቀመጠው የመመዘኛ መስፈርት መሠረት በሚደረገው የክህሎት ምዘና ግምገማና በሚሰጠው የምስክር ወረቀት ነው፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን በሞዱል መልክ ማደራጀት በትምህርትና ሥልጠና አሰጣጡ የተለያዩ የመግቢያና የመውጫ ዕርከኖችን በመፍጠር ከሁኔታዎች ጋር የሚለዋወጥ ለማድረግ ጠቃሚ አካሄድ ነው።

6.1.2 የተለያዩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ሞዱሎች ተጣምረው የረጅም ጊዜ ፕሮግራም በመሆን ወደ አንድ የብቃት ደረጃ የሚያደርሱና የተሟላ ትምህርትና ሥልጠናን የሚወክሉ ይሆናሉ፡፡ በሞዱል ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ ውስጥ አንድ ሠልጣኝ በራሱ ምክንያት ከፈለገ የረጅም ጊዜ የሥልጠና ፕሮግራሙን ከወዲሁ ማቋረጥና በሥራ ገበያ ውስጥ የተወሰኑ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ብቃት ይዞ ሊወጣ ይችላል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሠልጣኙ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ተመልሶ ሥልጠናውን በመቀጠል የቀሩትን ሞዱሎች በማሟላት ፕሮግራሙን ሊያጠናቅቅ ይችላል፡፡

6.1.3 አንድ ወይም በርከት ያሉ ሞዱሎች በአጭር ጊዜ ፕሮግራም ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሠልጣኙ በሥራ ገበያ ውስጥ ተፈላጊ ከሆኑ ብቃቶች ከፊሉን ወይም ወደ ረጅም ጊዜ የሥልጠና ክህሎት የሚወስደውን የመጀመሪያ ደረጃ ክህሎት ያገኛል ማለት ነው፡፡ በሙያ ዕድገታቸው ውስጥ ሠልጣኞች በሂደት የተለያየ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን እንደ አስፈላጊነቱ ከተለያዩ ሥልጠና ሰጪዎች በመከታተል በመጨረሻ አጠቃላዩን የብቃት ደረጃ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

6.1.4 አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ሞዱላራዊ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አደረጃጀት ለኢትዮጵያ አዲስ ንድፈ-ሃሳብ ነው፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና

ተቋማት ሞዱላራዊ ሥርዓተ ትምህርት እንዲቀርጹና የተቋማቱ ሥራ መሪዎች የሥልጠና ዕቅዶቻቸውን በዚያው መሠረት ለማስተካከል እንዲችሉ ለማድረግ አዲስ ክህሎት ያስፈልጋቸዋል፡፡ በመሆኑም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አካላት የሥርዓተ ትምህርት መመሪያን በማዘጋጀት፣ መምህራን ተጨማሪ ሥልጠና እንዲያገኙ በማድረግና በሞዱላራዊ ሥልጠና አደረጃጀት አቅምን በመገንባት ለማሰልጠኛ ተቋማቱ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

## 6.2 ከኩባንያዎች ጋር በትብብር የሚሰጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና

6.2.1 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥሞ እንዲሄድ ለማድረግ የሥራ ላይ ልምምድን ጨምሮ ከኩባንያዎች ጋር በትብብር የሚሰጠው ሥልጠና እየዳበረና ሥር እየሰደደ እንዲሄድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በትብብር የሚሰጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማለት የማሠልጠኛ ተቋማት ከኩባንያዎች ጋር ተባብረው የሚያካሂዱት የሥልጠና ሥልት ነው፡፡ የማሰልጠኛ ተቋማቱ የንድፈ ሃሳብና ለመነሻ የሚሆን የተግባር ትምህርት ሲሰጡ አብዛኛው የተግባር ትምህርት ብዙውን ጊዜ የሚሰጠው በድርጅቶች ውስጥ ነው፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት በከፍተኛ ደረጃ ባደገባቸው የአውሮፓ አገሮች የትብብር ሥልጠና ፕሮግራም የሚዘጋጀው እንደ መደበኛ የሥራ ላይ ሥልጠና ሆኖ በሠልጣኙና በኩባንያው መካከል በሚፈረም የሥራ ላይ ውል ነው፡፡

6.2.2 የሥራ ላይ ሥልጠና (ወይም በአጠቃላይ በትብብር የሚሰጥ ሥልጠና) ትልቁ ጥቅም ሥልጠናው ከሥራው ዓለም ጋር ቅርበት ያለው እንዲሆን ማስቻሉ ነው፡፡ ሠልጣኞቹም ከሥራው ዓለም ጋር በደንብ በመለማመድ በዕውኑ የሥራ ሁኔታ ተጨባጭ የሆነ የሙያ ክህሎት እንዲያገኙ ያግዛቸዋል፡፡ እስካሁን ያሉት ልምዶች በሙሉ የሚያሳዩት የሥራ ላይ ሥልጠና ሙያው የሚጠይቀውን ንድፈ ሃሳብና የተግባር ክህሎትን በማስጨበጥና ለሥራ አስፈላጊውን አመለካከት በማላበስ ረገድ በእጅጉ የተሻለ ውጤት እንደሚያስገኝ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሥራ ላይ ሥልጠና የሚሰጡ ድርጅቶች ከሠልጣኙ ጋር ስለሚተዋወቁ ሠልጣኞች ሥልጠናውን ከአጠናቀቁ በኋላ የሚቀጠሩበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ በትብብር በሚሰጥ ሥልጠና አማካኝነት ኩባንያዎቹም የየራሳቸውን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡ በመጨረሻም የሥራ ላይና የትብብር ሥልጠናዎች የማሰልጠኛ ተቋማት ውስብስብ ለሆኑ መሣሪያዎች ግዥ የሚያወጡትን ወጪ ስለሚያስቀሩና የሥልጠናውን ጊዜ ስለሚያሳጥሩ በተቋማት ብቻ ከሚሰጡ ሥልጠናዎች ጋር ሲነጻጸሩ ወጪ ቆጣቢ ናቸው፡፡

6.2.3 በአሁኑ ጊዜ ለጥቂት ወራት በሥራ ቦታ በሚደረግ የተግባር ልምምድ መልክ በትብብር የሚሰጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በመደበኛው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኘሮግራም ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ይህም የአገሪቷ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት አግባብነት ያለው እንዲሆን በማድረጉ ረገድ አንድ እርምጃ ወደፊት ያራመደ ነው፡፡ ሆኖም ግን ለኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የሚኖረውን ጠቀሜታ በሙሉ ለመጠቀም በትብብር የሚሰጥ ሥልጠና በበለጠ ሥር እንዲሰድ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም እንዲረዳ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪዎች አመቺ በሆነ መንገድ ሁሉ ከግል አሠሪዎች፣ ከንግዱ ህብረተሰብና ከአሠሪዎች ማህበራት ጋር በትብብር ስለሚሰጥ ሥልጠና ፕሮግራም አደረጃጀት መደራደርና ግንኙነት መፍጠር አለባቸው። በተጨማሪም ትናንሽ ኩባንያዎችና ጥቃቅን የንግድ ድርጅቶች ለበርካታ ሠልጣኞች የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ በመሆኑ በዚህ ረገድ ከእነዚህ ዘርፎች ጋር የሚደረገው ስምምነት የሚበረታታ ይሆናል፡፡ በመሠረቱ ግን በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪዎች የሚሰጠው ሥልጠና የሙያ ደረጃን እስከ ጠበቀና ለሠልጣኙ የሚያስፈልገውን ብቃት በሙሉ ወይም በከፊል የሚያስገኝ እስከሆነ ድረስ እንደ ኩባንያዎቹና ሠልጣኞቹ ፍላጎት የትብብር ሥልጠና ፕሮግራም ለማዘጋጀት ሙሉ ነፃነት ይኖራቸዋል።

6.2.4 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አካላት ትልልቅ ኩባንያዎች፣ ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራ ድርጅቶች ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ጋር እንዲተባበሩና የሥራ ላይ ሥልጠና ለመስጠት እንዲችሉ የማበረታቻ መንገዶች መቀየስ ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ ተሳታፊ ኩባንያዎችን ማስተዋወቅና የታክስ ማበረታቻ መስጠት እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

## 6.3 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ለራስ ሥራ ፈጠራ

6.3.1 ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ምሩቃን ወደ ሥራ ገበያ ለመግባት በተለይም በከተማ ቀመስና ገጠር አካባቢዎች በግል የራስ ሥራ መተዳደር አንዱ ጠቃሚ አማራጭ ነው፡፡ በራስ የግል ስራ ለመተዳደር ግን በአንድ በተወሰነ የሙያ ዘርፍ ከሚያስፈልገው ቴክኒካዊ ክህሎት በላይ ብቃትን ይጠይቃል። የተዋጣለት ኢንተርፕሪንየር ለመሆን ፣ በራስ መተማመን፣ ፈጠራ፣ የገበያን ሁኔታ በትክክል ማወቅ፣ መሠረታዊ የንግድ ሥራ አስተዳደር ክህሎትና የሚያጋጥሙ የችግር አዝማሚያዎችን መጋፈጥ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም አዲስ የንግድ ሥራን ለመጀመር የመሥሪያ ቦታ፣ ፋይናንስ የሥራ ፍቃድና ለሥራው የሚያስፈልጉ ሌሎች ግብአቶችን ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

6.3.2 እነዚህን ሁኔታዎች በማገናዘብ መሠረታዊ የኢንተርፕሪንየር ክህሎትና ተዛማጅ የንግድ ሥራ አስተዳደር ሥልጠና በሁሉም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኃላፊዎች ሥልጠና የሚሰጡ ተቋማት በዚህ መስክ ያለውን የዓለም አቀፍ ልምድ መሠረት አድርገው ተስማሚ የሥልጠና ፖኬጅ እንዲያዘጋጁ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

6.3.3 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የስልጠና መርሃግብር ሲያዘጋጁ የየአካባቢውን መካከለኛና አነስተኛ የንግድ ተቋማትን አሰራር ሂደት ግንዛቤ ዉስጥ እንዲያካትቱ ይበረታታሉ፡፡ ይህም ላምሳሌ አማራጭ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ፣መጠቀምንና የኢንተርፕሬነርሽፕና የ ትብብር ስልጠናዎች ለመካከለኛና አነስትኛ የንግድ ተቋማት ማዘጋጀትን ያካትታል፡፡ በተጨማሪም የ ቴ/ሙ ሃላፊዎች በባህላዊ ስልጠና አሰጣጥ ዐይነቶች የማጠናከርና የጥራት ስራዎች ብሎም የማስትዋወቅ ስራዎች መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም የአሰለጣጠን ስርዓት ወጣቶችን ለስራ ፈጣሪነት በቀልታፋ መልኩ እንደሚዘጋጃቸው መታወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

6.3.4 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የማያቋርጥ የቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ማዕከላት በመሆን የቴክኖሎጅውን ዕድገት ከግሉ ባለሀብት ጋር በመሆን የሚመሩና ችግር ፈቺ የሆኑ ጥናቶችን በማካሄድ ፕሮግራም የሚቀረፁ ማሠልጠኛዎች ይሆናሉ፡፡

## 6.4 በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂን ሥራ ላይ ማዋል

6.4.1 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥራትን ለማሳደግና ለሁሉም እንዲዳረስ ለማድረግ እንዲሁም በዘላቂነት እውቀት የሚቀሰምባቸውን ሁኔታዎች ለመፍጠር በትምህርትና ሥልጠናው አሰጣጥና ምዘና ላይ ዘመናዊውን የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን በሥራ ላይ ማዋል ጠቃሚ ዘዴ ነው፡፡ ይህንን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ሥልጠና፣ የማስተማርና የመማር ሂደት እንዲሁም የምዘና ማቴሪያሎችን የማዘጋጀት ተግባራትን በአነስተኛ ወጪ ማከናወን ይቻላል። ቴክኖሎጂው ሰልጣኙን መሠረት ያደረገ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅርቦትን ይደግፋል፤ የመረጃና እውቀት አቅርቦት ሁኔታን ያሻሽላል፤ ሠልጣኙን በራሱ ፍጥነትና ጊዜ ተምሮ እንዲመዘን ያስችለዋል፡፡ እ.ኤ.አ በ2002 በወጣው የኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ

ፖሊሲ መሠረት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

6.4.2 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ከተለመዱት የሥልጠና የትምህርት ዘዴዎች ጎን ለጎን ኤሌክትሮኒካል መሣሪያዎችን በመጠቀም (Blended learning) በብሌንድድ የመማር ስልት ለምሳሌ በ “E- learning” ትምህርት መስጠት የሚቻልበትን መንገድ እንዲያስተዋውቁና እንዲያመቻቹ ይበረታታሉ፡፡ አሁን የኢንተርኔትና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን ለማዳረስ ያልተቻለበትን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሲዲ ሮም (CD ROMS) እና የአካባቢ ኔት ዎርክ (Local Area Networks) አጠቃቀም እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡

6.4.3 የክልል መንግሥታትና ሌሎች የመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋም አካላት በተቋማቱ ውስጥ ተገቢው ቁሳቁስ መሟላቱንና መምህራን በትምህርትና ሥልጠና አሰጣጡ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን ማቀናጀት መቻላቸውን የማረጋገጥና ሠልጣኞቹም አዲሱን ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ አመራር የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የግልና መንግሥታዊ ያልሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የኤሌክትሮኒካል የመገናኛ ዘዴን (E-learing)ከትምህርት አሰጣጥ ዘዴያቸው ጋር አዋህደው እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ፡፡ ለዚህም እንዲረዳ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኃላፊዎች ሶፍትዌርና የኤሌክትሮኒክስ ትምህርት መሣሪያዎች የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርባቸዋል፡፡

6.4.4 በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የኢንፎርሚሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ አጠቃቀም ዳብሮ በትምህርት አሰጣጡ ላይ የኤሌክትሮኒክስ የማስተማር ዘዴ ሥራ ላይ እንዲውል የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አካላት ከክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አካላት ከኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ ተወካዮች ጋር በመሆን ተገቢውን ስትራቴጅ ይቀይሳሉ፡፡ ስትራቴጂው የኤሌክትሮኒክስ ማስተማሪያ ዘዴ ሞዱልን፣ የርቀት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን፣ የሰው ኃይል ልማትንና ሌሎች በዘርፉ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን ለማስፋፋት የሚረዱ ጉዳዮችን ያካተተ ሊሆን ይገባል፡፡

## 6.5 የሙያ ምክርና ድጋፍ

6.5.1 ሠልጣኞች በተለይም ወጣቶች ወደፊት የሚሠማሩበትን ሙያ መርጠው ትምህርትና ሥልጠናቸውን እንዲቀጥሉ ለማድረግ በሙያ መረጣ ምክር አገልግሎት

አሰጣጥ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ይደረጋል፡፡ ይህም በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የሚሰጠውን የትምህርትና ሥልጠና ዕድል ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም ያስችላል፡፡ የሙያ መረጣ ምክር አገልግሎት ከትምህርት ቤት መጀመር ይኖርበታል፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትም የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ሠራተኞችን አሰልጥነው እንዲመድቡ ይደረጋል፡፡ የአጠቃላይ ትምህርትን ጨርሰው የሚወጡትን ከወዲሁ ከሙያ ምርጫ ጉዳይ ጋር ለማስተዋወቅ ተቋማት ከትምህርት ቤቶች ጋር እንዲሁም ለአካባቢው ሠልጣኞች ስለሙያ መረጣ ምክር ለመስጠት መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከማህበራዊና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይሠራሉ፡፡ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚመደቡ የሙያ መረጣ ምክር አገልግሎት ሰጪዎች የሥራ ላይ ሥልጠናን በማመቻቸትና ወጣቱን ለሥራ ዓለም በማዘጋጀት ረገድ ትልቁን ሚና ይጫወታሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ምሩቃን በራሳቸው ሥራ መተዳደር እንዲችሉ ለማድረግ ድጋፍ ሰጪ ሆነው ይሠራሉ፡፡

6.5.2 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አካላት ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ተገቢው የሙያ ምክር ንድፈ ሃሳብ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋሉ፡፡ ይህም እያንዳንዱ ግለሰብ ተስማሚ ሙያ መምረጥ እንዲችል የዝንባሌ መመዘኛ ፈተና አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋትን ያካትታል፡፡

# 7. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን አቅም መገንባት

7.0.1 በሥራ ገበያ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ አመቺ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም በመቅረጽ ሥልጠና የሚሰጡ ውጤታማና ቀልጣፋ ተቋማት ለአዲሱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የጀርባ አጥንት ናቸው፡፡ በመሆኑም እንዲህ ዓይነቱን የመንግሥትም ሆነ የግል ተቋማት አቅም መገንባት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላት ቁልፍ ተግባር ይሆናል፡፡

## 7.1 የመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ተቋማትን ማጠናከር

7.1.1 ባለፉት ዓመታት መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን 10ኛ ክፍል አጠናቅቀው ለሚወጡ ተማሪዎች በስፋት ለማዳረስ የመንግሥት ተቋማት በብዛት እንዲስፋፉ ተደርጓል፡፡ ሆኖም የተቋማት መስፋፋት የተደረገው ለጥራት የሚገባውን ትኩረት ሳይሰጥ ነበር፡፡ አሁን የመንግሥት ትኩረት የማሰልጠኛ ተቋማትን በማጠናከር

ሥልጠናው በሥራ ገበያ ፍላጐት ያተኮረ፣ ተገቢው ጥራት ያለው ሆኖ ዕድሉን ላላገኙ ወገኖች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅርቦት ማስፋፋት ላይ ይሆናል፡፡

7.1.2 የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላት በየክልላቸው የሚከተሉትን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፤

- የማሰልጠኛ ተቋማት በዙሪያቸው ከሚገኙት አሠሪዎችና፣ ከትልልቅ፣ መካከለኛ፣ አነስተኛና ጥቃቅን የንግድ ድርጅቶች ጋር የጠበቀ የሥራ ግንኙነት በመፍጠር አቅማቸውን ማጎልበታቸውን፣
- በተቋማት የሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ምርጫ በክልሉ መንግሥትና በአካባቢው ባለው የሠለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ላይ መሠረት በማድረግ መሆኑን ፣
- በዘርፉ የሚደረገው የመንግሥት ኢንቨስትመንት ቅድሚያ የሚሰጠው በሥራ ገበያው ፍላጎት መሠረት መሆኑን፣
- መደበኛ ያልሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች፣ በተለይም በገጠር አካባቢ ለሚገኙ ለተለያዩ ተጠቃሚ ክፍሎችና በጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራ ዘርፎች ለሚሠሩ ሠራተኞች የሙያ ብቃት ቅድሚያ ትኩረት መሰጠቱን፣
- በአጠቃላይ ለሁሉም የማሠልጠኛ ተቋማት በተለይም ብቃት ያላቸውንና የቴክኖሎጂ አቅም ማከማቸትና ማስተላለፍ የሚችሉት ትኩረት ማግኘታቸውን፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የፋሲሊቲ አቅርቦት የአገር አቀፍ የሙያ ብቃት ደረጃን የሚያሟላ ሥልጠና ለመሥጠት በሚያስችል ሁኔታ መሻሻሉን ፣
- የሥልጠና፣ የማስተማሪያና የመማሪያ ማቴሪያሎች በበቂ መኖራቸውን፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራንና የተቋም አመራር አካላትን ጨምሮ ለዘርፉ የሰው ኃይል ልማትና አመራር ተገቢው ትኩረት ማግኘቱን፣
- የማሰልጠኛ ተቋማቱ ለሁሉም ያለ አድልዎ ክፍት መደረጋቸውንና በየተቋማቱ የልዩ ትምህርት ፍላጎት ላላቸው ወገኖች የሚያስፈልጉ ፋሲሊቲዎች የተሟሉ መሆናቸውን ፣
- በትምህርትና ሥልጠናው የሴቶች እኩል ተሳትፎ መረጋገጡን፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በአካባቢያቸው የኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ ወረርሽኝን በመከላከል ረገድ ሙሉ ተሳትፎ የሚያደርጉ መሆናቸውን፣

7.1.3 የመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ በአንድ በኩል ባሉት ተቋማት የሚሰጠው ሥልጠና ጥራትና አስተማማኝነት የተመጣጠነ እንዲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በየአካባቢው አቅርቦቱ እንዲኖር የማሰልጠኛ ተቋማቱ እንዲስፋፉ ይደረጋል ።

7.1.4 በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና መርሃ ግብሮች ውስጥ በመንግሥት የሚደረገው ኢንቨስትመንት ከግሉ ዘርፍ ጋር እንዳይደራረብና አላስፈላጊ የሀብት ብክንት እንዳይኖር በሀገር ደረጃና በየአካባቢው የሚታቀዱት አጠቃላይ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዕቅዶችን በማቀናጀት እና በግሉ ዘርፍና በመንግሥት የሚኖረውን አቅርቦት ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## 7.2 የግል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን ማጠናከር

7.2.1 ቀደም ሲል እንደተጠቀመው አስተማማኝ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዕድገት ለማምጣት መንግሥታዊ፣ መንግሥታዊ ባልሆኑና በግሉ ዘርፍ ተዋናዮች መካከል የሚኖረው መተማማን፣ ትብብርና መረዳዳት ዋናው ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ያሉት የየክልሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አስፈፃሚ አካላት በየክልላቸው በግሉና መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት በዘርፉ የሚደረገውን ኢንቨስመንት ማጠናከርና ማበረታታት ከዋነኛ ተግባሮቻቸው መካከል የሚጠቀሱ ይሆናሉ።

7.2.2 በዘርፉ በየደረጃው ያሉት የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላት ከፊል ኃላፊነቶችን በተዋረድ ለሚገኙ አስፈፃሚ አካላት አመቺ በሆነ መንገድ ውክልና በመስጠት በዘርፉ በግሉና መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት የሚደረገውን ኢንቨስትመንት ማጠናከር ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም የሚደረገው በተለይ፣

- መስፈርቱን አሟልተው ለሚቀርቡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ተገቢውን ሕግና ደንብ በመከተል በወቅቱና በተቀላጠፈ ሁኔታ እውቅና እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ተገቢ የመሬትና የማሰልጠኛ ህንፃ አቅርቦት ሁኔታ ማመቻቸት፣
- በክልሉ ስላለው የልማት ፕሮግራም ግንዛቤ እንዲያገኙ ከግሉና መንግሥታዊ ካልሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪ ተቋማት ተወካዮች ጋር በየጊዜው ውይይት ማድረግና መረጃ መስጠት
- የመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅርቦት ዕቅድ ድግግሞሽንና አላስፈላጊ መሻማትን እንዳይፈጥር በግሉ ዘርፍ ከሚኖረው አቅርቦት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ፣
- በግልና መንግሥታዊ ባልሆነ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የተሰማሩት ስለሥራ ገበያ፣ ሙያ ብቃት ደረጃ፣ በዘርፉ ስላለው የምርምር ውጤትና ከዘርፉ ጋር አግባብነት ስላለው ደንብና ስለ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ለመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚደረገው አቅም ግንባታ ለምሳሌም ለመምህራን የሚሰጡ ተጨማሪ ሥልጠናዎች፣ ለተቋማት

አመራርና ቦርድ አባላት የሚዘጋጁ የሥልጠና ኮርሶች ወ.ዘ.ተ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑና ለግሉ ተቋማት ሁሉ ክፍት መደረጋቸውን ማረጋገጥ፣

- በግሉና መንግስታዊ ያልሆኑ የግል ተቋማት የሥርዓተ ትምህርት መመሪያዎችንና የማሰልጠኛና ማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ለማግኘት አመቺ ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ያለውን ውስን ሀብት ኃላፊነት በተሞላበትና በቁጠባ እንዲጠቀሙ የሚያስችል መፍጠር፤

7.2.3 ከዚህም በተጨማሪ በዘርፉ ያሉት አስፈጻሚ አካላት መንግሥታዊ ላልሆኑና የግል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪዎች የፋይናንስ ማበረታቻ የሚያገኙበትን መንገድ በማጥናት መተግበር ይኖርባቸዋል፡፡

## 7.3 የሥርዓተ ትምህርትና የማሰልጠኛ / ማስተማሪያ መሣሪያዎች ዝግጅት

7.3.1 አገር አቀፍ የሙያ ደረጃዎች ሲዘጋጁ ይህንኑ መሠረት ያደረጉ አዳዲስ ሞዴል ሥርዓተ ትምህርቶች በክልሎች ይዘጋጃሉ፡፡ አዲሶቹ ሞዴል ሥርዓተ ትምህርቶች እንደ አሁኖቹ የፌዴራል ሥርዓተ ትምህርቶች የመተግበር ግዴታ ያለባቸው አይሆኑም፡፡ ይልቁንም እያንዳንዱ የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪ ተቋም የሙያ ብቃት ደረጃውን ተንተርሶ የራሱን ሠልጣኝ ፍላጎት መሰረት ያደረገ ሥርዓተ ትምህርት ይቀርጻል፡፡ የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣናት አዲስ የተዘጋጁት ሥርዓተ ትምህርቶች በክልሉ በሚገኙ የመንግሥትና የግል ተቋማት መተግበራቸው የማረጋገጥና ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

7.3.2 አሁን ያሉት አብዛኛዎቹ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪዎች በራሳቸው ደረጃውን የጠበቀ ሥርዓተ ትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራም ማዘጋጀት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ እንዳልሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የሙያ ብቃት ደረጃውን ተገቢ ወደ ሆነ ሞጁልና ውጤትን መሠረት ያደረገ ሥርዓተ ትምህርት መተርጎም እንዲችሉ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ በኩል በአቅም ግንባታ ረገድ ብዙ መሠራት ይኖርበታል። በአዲሶቹ የሙያ ደረጃ በተዘጋጀላቸው ሙያዎች የሥልጠናና የትምህርት መሣሪያዎች ዝግጅት ያለው ሁኔታ ተመሳሳይ ነው። ይህንን ድጋፍ ለማመቻቸትና ከፍተኛ ደረጃ ያለው ሥርዓተ ትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራም መዘጋጀቱን ለማረጋገጥ ሞዴል ሥርዓተ ትምህርትና የሥርዓተ ትምህርት መመሪያዎች፣ የሥልጠናና ትምህርት መሣሪያዎች ተዘጋጅተው ይቀርባሉ፡፡ እነዚህ መመሪያዎች በአገሪቷ ላሉት ሁሉም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅራቢዎች የሚዳረሱ ይሆናሉ፡፡

# 8. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት እውቅና አሰጣጥ

8.0.1 ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት እውቅና የመስጠቱ ሥርዓት ተቋማቱ ጥራትን እንዲያሻሽሉና አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ አጋዥና አበረታች በሆነ መልኩ የሚደራጅ ይሆናል፡፡

8.0.2 የዕውቅና አሰጣጥ ሁለት ዓላማዎች አሉት። እነዚህም፦

- ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የጥራት ደረጃ ማነፃፀሪያ ማስቀመጥ፣ ከተፈላጊው የጥራት ደረጃ ላይ ለመድረስ የሚያስችላቸውን የብቃት ደረጃ ማሳየትና ድጋፍ መስጠት እንዲሁም የውጤት ደረጃቸውን መገምገም፣
- በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ገበያ ግልፅነትን በማስፈን ሠልጣኞችን ደረጃውን ካልጠበቀ የሥልጠና አሰጣጥ መጠበቅ፣

8.0.3 በአሁኑ ወቅት የእውቅና አሰጣጥ የተመሠረተው በብሔራዊ ሥርዓተ ትምህርት መሠረት የጥራት አመልካች የሆኑት የመማሪያ ክፍሎችና ዎርክሾፖች መኖር፣ ተቋሙ ያሉት መምህራን ብዛትና የትምህርት ደረጃ በመሳሰሉት ቁሳዊና ሰብዓዊ ግብዓቶች ላይ ብቻ ነው። በአዲሱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ሥርዓተ ትምህርቱ ሁኔታዎችን ባገናዘበ መልኩ የሚቀረጽ በመሆኑ እነዚህ የጥራት አመልካቾች እንደገና ተጠንተው የሚዘጋጁ ይሆናሉ፡፡ በመሆኑም እውቅና ለመስጠት የሚያስችሉ የጥራት አመልካቾች ትኩረት የሚያደርጉት በተቋማቱ የውስጥ አመራር ጥራት አስተዳደር ሂደት ማለትም የሥራ ገበያን የማጥናትና ሥርዓተ ትምህርት የመቅረጽ አቅም፣ በሰው ኃይል አመራርና ልማት ስትራቴጅዎች እና በፋይናንስ አስተዳደር ሁኔታ ላይ ጭምር ይሆናል፡፡ የሌሎች አገሮች መልካም ተሞክሮ በማገናዘብ ተቋማት እንደየደረሱበት የጥራት አመራር ደረጃ የተለያዩ ደረጃዎች ያላቸው የዕውቅና አሰጣጥ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ ይህም ማለት በአገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጠውን የሙያ ብቃት ደረጃ መሠረት በማድረግ እያንዳንዱ ተቋም በራሱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም አዘጋጅቶ በመስጠት ረገድ ባለው አቅም መሠረት የተለያየ ደረጃ ያለው እውቅና መስጠት ማለት ነው፡፡

8.0.4 እውቅና የሚሰጠው ለግልም ሆነ ለመንግሥታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት ነው፡፡ እውቅና ያላቸው ተቋማት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ አስፈጻሚ አካላት የሚሰጡት ድጋፎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል። በዚህ መልኩ እውቅና ማለት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት አቅማቸውን በተጨባጭ

የሚገመግሙበት (ደካማ ጎናቸውን) ፣ ጥራትን በማሻሻል ረገድ የራሳቸውን ግብ በመጣል በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የሚሰጠውን ድጋፍ የሚያገኙበት ይሆናል፡፡ በመሆኑም በአንድ በተወሰነ ደረጃ የሚሰጠው እውቅና እንደ ጥራት ደረጃ ማረጋገጫ የሚታይና ተቋሙ አገልግሎቱን ለገበያ ለማቅረብ እንዲችል የሚረዳ ይሆናል፡፡

8.0.5 ሠልጣኞች ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት እውቅና ማግኘት ግዴታ ይሆናል፡፡ ከረጅም ጊዜ አኳያ የሥልጠናን ጥራት በሙያ ምዘናና በተቋማቱ ፈቃደኝነት ላይ ተመሥርቶ በሚያገኙት ዕውቅና ብቻ ማረጋገጡ ተገቢ ይሆናል፡፡

8.0.6 ዕውቅና የሚሰጠው በመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላት ሆኖ በተዋረድ የሚገኙ አካላት ተገቢውን አቅም አዳብረው ከተገኙ እንደ አስፈላጊነቱ በውክልና እውቅና እንዲሰጡ ማድረግ ይቻላል፡፡ በመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አካላት የሚሰጠው እውቅና በአገር አቀፍ ደረጃ ባለው የእውቅና አሰጣጥ ሥርዓትና ደንብ መሠረት ይሆናል፡፡ የዕውቅና ሰጪ ቦርዶች በየደረጃው የሚቋቋሙ ሲሆን የተቋማቱን ደረጃ የመገምገምና ተቋማቱ እንደደረሱበት ደረጃ ሁኔታ እውቅና የመስጠት ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡ የዕውቅና ሰጪ ቦርዶች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስሎች የሚቋቋሙ ሲሆኑ፣ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና አስተዳደር (ሥራ አስፈፃሚ) አካላት የተውጣጡ የቴክኒክ ባለሙያዎችን፣ የተቋማት ተወካዮችንና ሌሎች ባለድርሻዎችን (ለምሳሌ የንግድ ምክር ቤቶች አባላት) የቦርዶች አካላት ይሆናሉ፡፡

8.0.7 ቀደም ሲል የተጠቀሱትን መርሆዎችና የሌሎች አገሮችን ልምድ መሠረት በማድረግ የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲው የእውቅና አሰጣጥ ሥርዓትና ደንብ ያዘጋጃል፡፡ በዝግጅቱም ሂደት የመንግሥትና የግል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻዎች በተወካያቸው ወይም በማኀበራቸው አማካኝነት እንዲሳተፉበት ያደርጋል፡፡

8.0.8 የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ዕውቅና የተሰጣቸውን ተቋማት ዝርዝር ከክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላት ጋር በመተባበር እንደ አንድ የሥራ አመራር መረጃ ሥርዓት በመውሰድ መዝግቦ ይይዛል፡ በየዓመቱም ዝርዝራቸውን ያወጣል፡፡

# 9. የሰው ኃይል ልማት

## 9.1 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራን የቅድመ ሥራና ተከታታይ ሥልጠና

9.1.1 በከፍተኛ ደረጃ የሠለጠኑ፣ ብቃት፣ ፍላጎትና የፈጠራ ዝንባሌ ያላቸው፣ ከቴክኖሎጂ ለውጥ ጋር ራሳቸውን ፈጥነው ማስተካከልና ለተማሪዎቻቸው አመቺ የትምህርት ሁኔታ መፍጠር የሚችሉ መምህራን በማንኛውም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ውስጥ የጀርባ አጥንት ሆነው ያገለግላሉ፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት መንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራን ሥልጠና አሰጣጥን በተመለከተ መሠረታዊ ለውጥ በማድረግ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ የለውጥ ሂደቱ አላማ ተገቢውን ክህሎት አግኝተው የክህሎት ምዘናን ማለፍ የሚችሉ ሠልጣኞችን ማፍራት የሚችሉ መምህራንን መፍጠር ነው። በመሆኑም በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራን ስልታዊ የሆነ የቅድመ ሥራና ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል፡፡ በዚሁ መሠረት በመደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም በየደረጃው ለሚሳተፉ መምህራን የተለያየ ደረጃ ያለው ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

9.1.2 የመምህራን አቅርቦትን ከተገቢው የቅድመ ሥራና ቀጣይ ሥልጠና ጋር ለማሳደግ ይቻል ዘንድ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራን ሥልጠና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ እየተጠናከረ ሲሆን፣ አዳዲስ መርሃ ግብሮችም ተዘጋጅተዋል። ከዚህም በተጨማሪ ባሉት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ለቴክኒክና ሙያ መምህራን ማስልጠኛ የሚሆኑ የትምህርትና ሥልጠና ፋኩሊቲዎች ወይም የትምህርት ክፍሎች ይደራጃሉ።

9.1.3 ቀደም ሲል የነበረው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራን የሙያ ደረጃ አወቃቀር እንደገና ተሻሽሎ አዲስ የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብር ይጀመራል፡፡ አዲሱ የሙያ ደረጃ አወቃቀር የሚመሠረተው በምህንድስና ሙያ ደረጃና ሌሎች በተሻሻሉ የዲግሪ መርሃ ግብሮች መሠረት ሆኖ የሥነ-ትምህርት አሠጣጥ ዘዴና ተዛማጅ ሞዱሎችን ያካተተ ይሆናል፡፡ አዲሱ የመጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራም ትኩረት የሚያደርገው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራን የተግባር ብቃትን በማጠናከርና መምህራን ለተግባራዊ ሥራ ትኩረት እንዲኖራቸው በማድረግ ላይ ይሆናል፡፡ በሥልጠና ወቅት በፋብሪካዎች በመገኘት ተደጋጋሚ የሥራ ላይ ልምምድ ይደረጋል። የሥርዓት ትምህርቱ በሞዱል መዘጋጀት ሠልጣኞች እንደ አስፈላጊነቱ ወደ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህርነት ሥልጠና እንዲገቡና ወጥተው ወደ ሥራ ከተሠማሩ በኋላ እንደገና ተመልሰው የመምህርነት ሥልጠናቸውን እንዲከታተሉ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

9.1.4 የመምህርነት ትምህርትና ሥልጠና የተለያየ ትምህርት እና ሙያ ላላቸው ሰዎች ክፍት ይደረጋል። በዚህ ረገድ የቴክኒክ ብቃትና የሥራ ልምድ ያላቸው ሰዎች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህርነት ተፈላጊ ይሆናሉ፡፡ እነዚህን ባለሙያዎች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህርነት የዲግሪ መርሃ-ግብር ሥልጠና ብቃት እንዲኖራቸው ማድረግ የሚያስችሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለዚሁ የተመረጡ የቅድመ ዝግጅት ማሚያ ኮርሶችን እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ በተለይም፣

- የተወሰነ ዓመት ተግባራዊ ልምድ ያገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ምሩቃንና ሌሎች በሥራው ዓለም ተግባራዊ ክህሎት ያዳበሩ ሰዎች ወደ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህርነት ሥልጠና እንዲገቡ ይበረታታሉ፡፡ ወደ ከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት መግባት እንዲቻል የቀለም ትምህርታቸውን ለማሻሻል የሚያስችል የማሚያ ኮርስ ይሰጣል፡፡ ልዩ የትምህርት ደረጃ ወጥቶ ወደ ከፍተኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሚገቡበት ሁኔታም ይቃኛል፡፡
- ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ለሚወጡና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መሠረት ለሌላቸው የልምድ ባለሙያዎች ወደ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራን ሥልጠና ለመግባት የሙያ ምዘናን ማለፍ እንደ ቅደመ ሁኔታ ይቀመጣል።

9.1.5 አሁን ያሉትን የቴክኒክና ሙያ መምህራን ብቃት ለማሳደግና በህይወት ዘመናቸው ሙሉ ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ የቀጣይ ትምህርት ማሻሻያ ሥርዓትና ሥልጠና መርሃ-ግብር በማዳበር ላይ ትኩረት ይደረጋል፡፡ ቀጣይ ሥልጠና የሚያስፈልገው መምህር ተግባራዊ ክህሎትን ፣ የሙያ ንድፍ ሃሳብንና ቴክኖሎጂን እንዲሁም የማስተማር ሥነ ዘዴን፣ የትምህርት አሰጣጥ ብቃትን ጨምሮ ሌሎች የሚያስፈልጉ ብቃቶችን ጨምሮ ትምህርትና ሥልጠና የሚወስድ ይሆናል፡፡ ቀጣይ ሥልጠና የመንግሥትንም ሆነ የግል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት መምህራንን በተመሳሳይ ሁኔታ የሚያሳትፍ ይሆናል፡፡

9.1.6 መደበኛ ትምህርት ለሌላቸው የቴክኒክና ሙያ መምህራን ለምሳሌ ያህል በማህበረሰብ ክህሎት ማሻሻያ ማዕከላት የሚያስተምሩ፣ በኩባንያዎች ውስጥ ለሚገኙ ሙያዊ ድጋፍ ሰጪዎችና አስልጣኞች፣ ለዕድ ጥበብ ሙያተኞችና ሌሎች መደበኛ ባልሆነ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅርቦት ላይ ለተሰማሩ ሰዎች በፍላጎታቸው መሠረት የተዘጋጀ የዲግሪ መርሃ-ግብር ያልሆነ ቀጣይ ሥልጠና የሚሰጥ ይሆናል ፡፡

9.1.7 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራንን ሥልጠናና ቀጣይ ሥልጠና ጥራት ለማሻሻል የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮች በቅርብ የሚጀመሩ ይሆናሉ፡፡ይህም በዩኒቨርሲቲዎች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የምርምር መርሃ ግብሮችን ማቋቋም የሚያካትትና ትምህርትን ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ምርምር ጋር ለማዋሃድ የሚያስችል ይሆናል፡፡

9.1.8 ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ የሚኖረው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራን ሥልጠናና ቀጣይ ሥልጠና ኃላፊነት በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ይሆናል፡፡ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራን ሥልጠናና ቀጣይ ሥልጠና ዕቅድ ዝግጅትና ትግበራ ላይ በከፍተኛ ትምህርትና በአገርአቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኤጀንሲ መካከል ቅርብ የሥራ ትብብር መኖሩን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስልት ይቀየሳል፡፡ በየክልሎች ለሚገኙ የተለያዩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራን የሚያስፈልገውን ቀጣይ ሥልጠና ለማመቻቸት የመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላት ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ከኩባንያዎች፣ በትምህርትና ሥልጠና አሰጣጣቸው ልቀው ከሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ድርጅቶች ጋር ግንኙነት የመፍጠር ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 9.2 ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስተዳደር የሰው ኃይል ልማት

9.2.1 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራን ብቃት ከመገንባት በተጨማሪ የተቋማትን የአስተዳደርና ማኔጅመንት ሠራተኞችና ሌሎች በካውንስልም ሆነ በቦርድ አባልነት በተለያየ ደረጃ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስተዳደር የሚሳተፉትን ባለሙያዎች ብቃት ለመገንባት ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፤ በቂ ግብዓትም ይመደባል። በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ሥልጠናና የግንዛቤ ማሳደጊያ ፕሮግራሞች ይቀረፃሉ፡፡

9.2.2 የሰው ኃይል ልማት ሥራው የሚከተሉት ልዩ ትኩረት የሚሹ ወገኖች ያካትታል፣

- በፌዴራልና በክልል ደረጃ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስል አባላት፡
- በፌዴራል፣ በክልል፣ ዞንና ወረዳ ደረጃ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስተዳደር ሥራ አስፈጻሚ አካላት ሠራተኞች፣
- የሙያ ደረጃና ምዘና የሚያዘጋጁ የሥራ ክፍሎች ሠራተኞች፣
- በሙያ ምዘና ሥርዓቱ ውስጥ ፈተና በመስጠት የሚሳተፉ ባለሙያዎች፣

- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ሃላፊዎች
- የቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ተቋማት የሥራ አመራር ቦርድ አባላት፣

## 9.3 ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሠራተኞች አመቺ የሥራ ሁኔታን መፍጠር

9.3.0.1 ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ለረጅም ዓመታት በተሰጠው ዝቅተኛ አመለካከት ሳቢያ የሥራ ሁኔታው የሚስብ ባለመሆኑ ከፍተኛ የሙያ ደረጃና የሥራ ፍላጎት ያላቸው ባለሙያዎች ወደ ዘርፉ ለመሳብ ሳይቻል ቆይቷል፡፡ በመሆኑም በዚህ ስትራቴጂ የተቀመጠውን የዘርፉን ማሻሻያ ሥራ በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ባለሙያዎች አመቺና የሚስብ የሥራ ሁኔታ መፍጠር ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው፡፡ በዚሁ ረገድ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ባለሙያዎችን ለመሳብ የሚያስችል ደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

9.3.0.2 ካልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓት መተግበር ጋር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የፋይናንስ ሥራ አመራር ኃላፊነት እየጨመረ ሲሄድ ተቋማቱ የተሻለ የሥራ አፈጻጸም ለሚያስመዘግቡ ሠራተኞች ማበረታቻ ለመስጠት ሠፋ ያለ የፋይናንስ ማሻሻያ መብት (Autonomy) ይኖራቸዋል፡፡

9.3.0.3 በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አካላት በፈቃደኝነት ለሚያገለግሉ ባለድርሻዎች ተገቢው ማበረታቻ ይሰጣል፡፡ ይህም ተግባራዊ የሚሆነው በተለያየ ደረጃ ለሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስል አባላት፣ የተቋማት ሥራ አመራር ቦርድ አባላት፣ የሙያ ደረጃና የሙያ ምዘና አዘጋጆችና ፈተና ሰጪ የሥራ ክፍሎች ይሆናል፡፡

# 10. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፋይናንስ ስልት

10.0.1 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን ጥራትን ለማጐልበትና የቅበላ አቅምን በዘላቂነት ለማሳደግ አዲስ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፈንድ ሥርዓት ይቀየሳል፡፡ ወደፊት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የሚፈጠርን የመዋዕለ ንዋይ እጥረት ለመቅረፍ ጥራትን በማያዛባ ሁኔታ የወጪ ቁጠባ ስልቶች እና የውጪ መዋዕለ-ንዋይ የሚገኝበት እንዲሁም በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብሮች የገቢ ምንጮች የሚስፋፉበት መንገድ ይቀየሳል፡፡

10.0.2 ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘላቂነት ያለው ተጨማሪ መዋዕለ-ንዋይ የሚገኝበት አንዱ መሰረታዊ መንገድ በዘርፉ የግል ኤንቨስትመንትን ማበረታታት ነው፡፡ ከላይ በስትራተጂው ሌሎች ክፍሎች እንደተጠቀሰው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት በዘርፉ የግል መዋዕለንዋይና የኩባንያዎች ተሳትፎ እንዲጎለብት ያበረታታል፡፡ ለዚህም በዘርፉ ለሚደረገው የግል መዋዕለነዋይ የፋይናንስ ማበረታቻ ሥርዓቶች ይዘጋጃሉ፡፡

10.0.3 ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሚያስፈልገው የመዋዕለ ንዋይ መሠረት የሚሻሻልበት ሌላው መንገድ የሥልጠና አሰጣጥ ቅልጥፍናን በማሳደግ ወጪን መቆጠብ መቻል ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የሥራ አመራር መዋቅርና አሠራርን ዘመናዊ በማድረግና ለተቋማቱ ተጨማሪ የፋይናንስ ሥራ አመራር ኃላፊነቶችን በመስጠት በተቋማት የሚገኘውን አቅም አጠቃቀም ማሳደግ ይቻላል። ለምሳሌ እንደ ሁኔታው አመቺ የሆነ የባለሙያ ምልመላ ደንቦችን እንዲጠቀሙ በማድረግ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን የአሠራር ቅልጥፍና በከፍተኛ ደረጃ የማሳደግ ዕድል እንዲኖር ማድረግ ይቻላል፡፡ በመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሥራ አፈጻጸም ውጤትን መሠረት ያደረገ የመዋዕለ ንዋይ አመዳደብና የሥራ አመራር ሥርዓት ተግባራዊ የሚደረግበት መንገድ ይፈለጋል፡፡

10.0.4 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ጥራትን ከማሳደግ ጎን ለጎን አሁን ካለው ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረገ የሥልጠና አሠጣጥ ሥርዓት ይልቅ ወጪ ቆጣቢ የሆኑ አማራጭ የሥልጠና አሰጣጥ ስልቶችን ያበረታታል፤ ያጠናክራል፡፡ በሌሎች አገሮች የተካሄዱ የንጽጽር ጥናቶች እንደሚያሳዩት በተቋማት ከሚሰጠው ሥልጠና ይልቅ በተጨባጩ የሥራ ዓለም የሚሰጠው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብር ወጪ አነስተኛ ነው፡፡ በመሆኑም በትብብር የሚሰጠው የትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብር በተለይም የሥራ ላይ ልምምድ ሥልጠና መርሃ-ግብር ቀስ በቀስ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የነፍስ ወከፍ ወጪን ለመቀነስ ይረዳል፡፡ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ በትብብር ለሚሠሩና በኩባንያዎች ውስጥ ሥልጠና ለሚሰጡ ማበረታቻ ይሰጣል፡፡

10.0.5 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓትን ከሁኔታዎች ጋር ተለዋዋጭ በማድረግ በኩል ከሚደረጉት ማሻሻያዎች በተጨማሪ የተቋሚትን የፋይናንስ ምንጭ ማስፋፋት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በመንግሥት ለሚሰጠው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናና በዘርፉ የሚፈለገውን የአስተዳደርና የሥራ አመራር መዋቅርና ድጋፍ

ለመስጠት እንዲቻል በቂ መዋዕለ-ንዋይ የሚገኝበትን መንገድ ማፈላለግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የፋይናንስ ምንጭን ለማስፋፋት መንግሥት ከሚመድበው በጀትና ከውጭ ለጋሾች ከሚሰጥ ድጋፍ በተጨማሪ የሥልጠና ተጠቃሚዎች ከፍተኛ ጫና በማይፈጥር መንገድ ቀስ በቀስ ወጪ እንዲጋሩ ይደረጋል፡፡

10.0.6 አሠሪ ድርጅቶች ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ወጪ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ የነፃ ትምህርት ዕድል፣ የቁሳቁስ ስጦታና የሌሎች የማበረታቻ መንገዶች ይዘረጋሉ፡፡

10.0.7 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን የገቢ ምንጭ ማጠናከር ሌላው ለትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ የሚያስፈልግ መዋዕለ ንዋይ ድጋፍ ማሰባሰቢያ ስልት ነው። አሁን ያሉትን መሠረታዊ የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች ለምሳሌ ያህል በሠልጣኞች የተመረቱ ምርቶችን በመሸጥ፣ የንግድ ሥራዎችን በማካሄድ ወይም የተቋማትን ፋሲሊቲዎች በማከራየት የሚገኘውን ገቢ የተቋማትን የሥራ አመራር አቅምና የግብይት ክህሎትን በማሳደግና የውስጥ ገቢ የፋይናንስ ምንጭ አጠቃቀም ደንቦችን በማሻሻል ማሳደግ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ተቋማት ገቢ የማስገኘት ጥረታቸውን እንዲያሳድጉ ለማበረታታት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላት ተጨማሪ የበጀት እና ወይም የማበረታቻ መንገዶችን ሊቀይሱ ይችላሉ፡፡ ሆኖም የውስጥ ገቢ መሰረታዊ የተቋማት የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ ተቋማት ለተገልጋዮች ቀጣይነት ባለው መንገድ ያላቸውን ቴክኖሎጂ የሚያስተላልፉበት ሥልት ይሆናል፡፡

10.0.8 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ሥራ አመራር ቦርዶች የተቋማትን የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች መከታተል፣ ድጋፍ መስጠትና መቆጣጠር ይኖርባቸል፡፡ ይህ ቁጥጥር የአሠራር ባህርይንና አፈጻጸምን እንዲሁም የገቢውን አጠቃቀም ይጨምራል፡፡ እንደ አጠቃላይ የአሠራር መርህ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ተቋማትን ዋና ተግባራቸው ከሆነው ሥልጠና የመስጠት ትኩረት ውጭ ሊያደርጋቸው አይገባም።

10.0.9 የተለያዩ የፋይናንስ ማፈላለጊያ ስልቶች የበለጠ የሚጠናከሩበትንና ተግባራዊ የሚደረጉበትን እንቅስቃሴ በተመለከተ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላት አስፈላጊውን ሁሉ ይፈጽማሉ።

# 11. የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ምርምር፣ ክትትልና ግምገማ

## 11.1 የጥናትና ምርምር አቅምን መገንባት

11.1.1 በአሁኑ ወቅት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የትምህርትና ሥልጠና ወጪን፣ የሥራ ገበያ ዕድገትን፣ የተቋማትን በተለይም በግል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን የሥልጠና አቅርቦት ሥርዓትንና ያመጡትን ለውጥ፣ ባለድርሻዎች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ላይ ስላላቸው አመለካከት ወ.ዘ.ተ አስመልክቶ አስተማማኝ መረጃ ያለመኖር ችግር ውስጥ ይገኛል። ሆኖም እነዚህ መረጃዎች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የሚኖረውን ዕቅድ፣ ክትትልና አዲስ ግኝት ለማሳወቅ አስፈላጊ ናቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ ያለው የምርምር አቅም ባለመዳበሩ ምክንያት ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጋር የተዛመዱ የጥናትና ምርምር አገልግሎቶች የሚሰጡት በዓለም አቀፍ ባለሙያዎች ነው፡፡ በዚህ ረገድ ቀስ በቀስ ራስን ለመቻል በአገራችን ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ትንተና ምርምር አቅም መገንባት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

11.1.2 በዘርፉ የምርምር ፍላጎትን ለመለየት ፣ የምርምር ሥራዎችን ለመምራትና ከምርምሩ የሚገኘውን ውጤት ለመጠቀምና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዕቅድ ዝግጅት ሂደት ውስጥ ለማንጸባረቅ እንዲቻል በፌዴራልና በክልል ደረጃ በሚገኙ የዘርፉ አስፈፃሚ አካላት ጥናትና ምርምር የማካሄድ አቅማቸው እንዲገነባ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም በአቅም ግንባታ ሚኒስቴር አማካይነት ከሚካሄዱ ሌሎች የጥናትና ምርምር ሥራዎች ጋር በማቀናጀት በፌዴራልና በክልል ደረጃ በሚገኙ የዘርፉ አስፈጻሚ አካላት ውስጥ የጥናትና ምርምር የሥራ ክፍል እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡ የጥናትና ምርምር የሥራ ክፍሎች ሥልጣንና ተግባር የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡

- ተጠሪ በሆኑበት አካባቢ ያሉ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መረጃዎችን ይለያሉ፣ ያጠናቅራሉ፣ ያስተዳድራሉ፡፡
- የጥናትና ምርምር ውጤቶችን አሳትሞ በማውጣት ፍላጐት ላላቸው ባለድርሻዎች መረጃ ይሰጣሉ፣
- በማንኛውም የዕቅድ ዝግጅትና ክትትል ሂደት ተገቢ መረጃዎች ከግምት ውስጥ መግባታቸውን ያረጋግጣሉ፣
- የጥናትና ምርምር ፍላጎትን ይለያሉ፣
- ለጥናትና ምርምር ተቋማት የምርምር ፕሮጀክቶችን ይሰጣሉ፣ ሥራውንም ይከታተላሉ፣

11.1.3 እነዚህ የጥናትና ምርምር ክፍሎች ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሥራ ገበያ ሁኔታን በመቆጣጠርና የሥራ አመራር መረጃን ሥርዓት በማቋቋም ረገድ እንደ ማዕከል ሆነው ያገለግላሉ፡፡

11.1.4 ከዚህም በተጨማሪ የዘርፉ አስፈፃሚ አካላት በሌሎች በተለይም በቴክኒክና ሙያ ትምህርትናሥልጠና መምህርነት ሥልጠና ላይ በተሰማሩ ዩኒቨርሲቲዎች፣ በልህቀት ማዕከላት (center of competence)፣ በኮሌጆችና በሌሎች ማሰልጠኛ ተቋማት የሚደረጉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥናትና ምርምር ሥራዎች እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡ በዚህ ረገድ ከሚወሰዱ እርምጃዎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- የሰው ኃይል አቅም ግንባታን አስመልክቶ ስለሚሰጠው ድጋፍ ከከፍተኛ ትምህርት ዘርፍና ጉዳዮ ከሚመለከታቸው ዩንቨርስቲዎች፣ ኮሌጆችና ማዕከላት ጋር ግንኙነት ያደርጋሉ፣
- ለጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶች በጀት መመደብና ለአገር ውስጥ ዩኒቨርስቲዎችና ሌሎች የጥናትና ምርምር ተቋማት የምርምር ፕሮጀክትቶችን ኮንትራት ይሰጣሉ።
- በዓለም አቀፍ ባለሙያዎች የሚደረጉ ማናቸውም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥናትና ምርምሮች በአገሪቱ የምርምር አቅምን ለመገንባት መዋሉን ለማረጋገጥ የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶች አግባብነት ባለው በአገሪቱ የሚገኝ ተቋም ውስጥ እንዲከናወን ማድረግና ኢትዮጵያዊያን ባለሙያዎች ከዓለም አቀፍ ባለሙያዎች ጋር እንዲሠሩ ይመደባሉ።
- የምርምር ፍላጎቶችን መለየትና ቀደም ተከሎችን ማውጣት፣ የአገሪቷ የጥናትና ምርምር ተቋማት የሚመሩበት የመካከለኛ ጊዜ የምርምር ዕቅድ ማዘጋጀት ናቸው።

## 11.2 የሥራ ገበያ ክትትልና ትንበያ

11.2.1 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን ከሥራ ገበያ ፍላጎት አንፃር መቃኘት እንዲቻል በቅድሚያ የሥራ ገበያ መረጃን መተንተንና መገንዘብ ይገባል። የሥራ ገበያ መረጃ በአቅርቦት በኩል ያለውን ማለትም የሕዝብ ብዛት ፣ትምህርት ጨርሰው የሚወጡትን፣ የሥራ አጦች ቁጥርን በክልልና በሙያ ወዘተ... እንዲሁም የአሁኑንና የወደፊቱን የገበያ የሠለጠነ ሰው ኃይል ፍላጐት ማለትም የክህሎት ክፍተት፣ የሥራ ቅጥር ሁኔታ በኢኮኖሚ ዘርፍና የሥሪ መስክ፣ የሚፈጠር ገበያ፣ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችንና በገጠሩ ያለውን ኢኮኖሚያዊ አጋጣሚ ወዘተ... ያጠቃልላል።

11.2.2 የሥራ ገበያ መረጃና ትንበያን አስመልክቶ አግባብነት ያላቸው በርካታ መረጃዎች በተለይም በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ፣ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣

በክልል ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራ ኤጄንሲዎችና ሌሎች ተቋማት ይገኛሉ፡፡ እነዚህን የገበያ ጥናቶች ማሻሻል ሳይደረግ እንዳለ በመውሰድ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት መጠቀም የሚቻል አይደለም። ስለሆነም ያለውን መረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ዕቅድ ዝግጅትና ክትትልን አላማ ለማሳካት በሚጠቅም መልክ መተንተን ይኖርበታል፡፡

11.2.3 ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሚደረገው የሥራ ገበያ ጥናት የማያቋርጥ/ ቀጣይነት ያለው ሂደት ሲሆን ይህም በሥራ ገበያው የሚከሰተውን ለውጥና ተፈላጊ የትምህርትና ሥልጠና ደረጃ ከወዲሁ በማወቅ አስፈላጊ የሥርዓት ትምህርትና ሥልጠና ዕቅድ ለውጥ ለማድረግ፣ የሙያ ደረጃን ለማሻሻልና አዳዲስ የሙያ ደረጃዎችን ለማውጣትና ተገቢውን የሥልጠና አቅም ለማዳበር ያስችላል።

11.2.4 በመሆኑም የጥናትና ምርምር አካላት ከክልልና ከፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጄንሲዎች ጋር በመተባበር ተጨባጭ የሆነና ተከታታይነት ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሥራ ገበያ ክትትል ሥርዓት መቅረጽ ይጠበቅባቸዋል። ይህም የሚደረገው ከባለድርሻዎችና የሥራ ገበያ መረጃ ባለቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር፣ በገበያ ክትትል ጥናት የሚገኘውን ውጤት በመጠቀም የሥራ ገበያ አዝማሚያን ከወዲሁ ለማወቅ የሚያስችሉ በዝቅተኛ ወጪ የሚገኙ መሣሪያዎችን በመጠቀም ይሆናል፡፡

## 11.3 የሥራ አመራር መረጃ ሥርዓት

11.3.1 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዕቅድን ለማዘጋጀት ስላሉት (ማለትም ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ብዛት ፣ ለሚሰጡ መርሃ-ግብሮች፣ ያሉ መምህራንና ሌሎች ሠራተኞች ወ.ዘ.ተ) ሁኔታና ስለተቋማት ውጤቶች (ማለትም በየተቋማት የሚገቡት ሠልጣኞች ብዛት ፣ የምሩቃን ብዛት፣ የሙያ ብቃት መመዘኛ ፈተና የተቀበሉና ያለፉ ሠልጣኞች ብዛት) አጠቃላይ ስዕል ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ያሉ የሙያ ደረጃዎችን ፣ የመመዘኛ ፈተናዎችንና የፈተና ውጤቶችን በመረጃ መልክ ማጠራቀም ያስፈልጋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈላጊ የሆነውን የሥራ አመራር መረጃ ለማሰባሰብና ለማደራጀት ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ ይህንን ጥረት አጠናክሮ መቀጠልና አጠቃላይ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠናን የሥራ አመራር መረጃ ማጠናከር ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡

11.3.2 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥራ አመራር መረጃ ሥርዓት በተለያየ ደረጃ ካሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥራ አመራር ሥርዓት የሚገኘውን መረጃ አሰባስቦ የሚጠቀም ይሆናል፡፡ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥራ አመራር መረጃ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑና አስተዋጽዎ የሚያደርጉ ሁሉ አዲሱን ሥርዓት ተግባራዊ እንዲያደርጉና እንዲጠቀሙ ለማድረግ ሥልጠና ይሰጣል፡፡

## 11.4 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ክትትልና ግምገማ

11.4.1 በዚህ ስትራቴጂ የተቀመጠውን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማሻሻያ ሂደት ለመከታተልና የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከወዲሁ ለመለየት የዘርፉ የሥራ አስፈፃሚዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ይዘረጋሉ። ይህም የሚረዳው፣

- የስትራቴጂውን ዓላማ የውጤት አመልካቾች መስፈርቶች ለመተርጎምና የውጤት አመልካቾቹ መሟላታቸው የሚረጋገጥበትን ስልት ለመለየት፣
- የውጤት አመልካች መስፈርቶቹ ከአገር አቀፍ የዕድገት አመልካቾች ጋር በተለይም ከፈጣን የኢኮኖሚ እድገትና የድህነት ቅነሳ መርሃ-ግብር ውጤት አመልካቾች ጋር መጣጣማቸውን ለማረጋገጥ ፣
- የሥራ ሂደትን በትክክል ለማወቅና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥራ አመራር መረጃ ሥርዓት አማካይነት አስተማማኝ መረጃ ለማሰባሰብ ፣
- እንደአስፈላጊነቱ የመነሻ ጥናት እንዲካሄድ በማድረግ መረጃዎች በየጊዜው ወቅታዊ መሆናቸውን ለመቆጣጠር፣ ይሆናል፡፡

11.4.2 የዘርፉ አካላት የክትትል ውጤቱን በማሰባሰብ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥራ ሂደት ሪፖርት እንዲያቀርቡና በየዓመቱ ሪፖርቱ ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋሉ፡፡

# 12. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስተዳደርና ሥራ አመራር ሥርዓት

12.0.1 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማሻሻያ በዘርፉ ብቃት ያለው ባለሙያ ለማፍራት ካለው ጉጉት አንፃር የተወጠነ በመሆኑ ራዕዩን ለማሳካት ብቃትና ቁርጠኝነት ያለው ጠንካራ አስተዳደርና ሥራ አመራር ያስፈልገዋል፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መዋቅራዊ አደረጃጀትም ሥርዓቱ ብቃት ያለውና በዘርፉ ያሉ የተለያዩ ሙያዎችንና ክህሎቶችን መሠረት ያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ባለድርሻዎች ውጤት

የሚያስገኝ ተጨባጭ ሚና እንዲጫወቱ ይደረጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በየጊዜው የሚለዋወጠውን የህብረተሰቡን የትምህርትና ሥልጠና ፍላጎት ለማሟላት ሥርዓቱ ተለዋዋጭና ከተለያዩ ዘርፎች ፣ ድርጅቶችና ፍላጎት ካላቸው ቡድኖች ጋር ግኑኝነት ለመፍጠር አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

12.0.2 በመተግበር ላይ ያለው ተቋማዊ መዋቅር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን እንደ አንድ የትምህርትና ሥልጠና ንዑስ ዘርፍ ያደረገ በመሆኑ ባለድርሻዎች በዘርፉ ያላቸውን ተጽእኖ በእጅጉ የገደበና ለተለያዩ ዘርፎች ፍላጎት ምላሽ የሚሰጥ አልነበረም፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስል አማካሪ አካል ሆኖ ከመሥራት ውጪ ተጠያቂነትን ያካተተ የተግባር ኃላፊነት አልነበረውም፡፡ ይህም ሁኔታ መንግሥታዊና የግል ዘርፉ ባለድርሻዎች ለዘርፉ ዕድገት ጊዜንና መዋዕለ ንዋይን በመመደብ ረገድ በሚኖራቸው ተነሳሽነትና ዝግጁነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድራል፡፡ በዘርፉ የሚገኙ ውሳኔ ሰጪ አካላት የሚያወጡት ፖሊሲና የተግባር እንቅስቃሴም ከህዝቡ ፍላጎትና ከአገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር በተከታታይነት ተጣጥሞ እንዲሄድ የሚያደርግ አልነበረም፡፡ በማደግ ላይ ባሉና ባደጉ አገሮች ያለው ልምድ የሚያሳየው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ስኬታማ የሚሆነው ባለድርሻዎች ወሳኝ በሆኑ የፖሊሲ አቅጣጫና የጥራት ሥራ አመራር አፈጻጸም ላይ ሰፊ ተሳትፎ ሲያደርጉ ነው፡፡ በሌሎች አገሮች በተለይም በአፍሪካ ሌሎች የዘርፉ ጉዳይ የሚመለከታቸውን አካላትና ህብረተሰቡን ይጨምራሉ፡፡ ይህም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪ ድርጅቶችንና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ይጨምራል፡፡ እነዚህ ባለድርሻዎች ውጤታማ በሆነ መልክ መሥራት የሚችሉት በዘርፉ የሚያሳድሩት ተጽእኖ ጠንካራና የማያሻማ ሆኖ ሲገኝ ብቻ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

12.0.3 ቀደም ሲል የነበረው ሌላው ችግር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ከትምህርት ዘርፍ ጋር በነበረው የጠበቀ ግንኙነት ሳቢያ ከሌሎች የዘርፉ ተጠቃሚዎች ጋር ውጤታማ ግንኙነት ከመፍጠርና ፍላጎታቸውን ከማሟላት አኳያ አቅሙን ገድቦት መቆየቱ ነው። የትምህርት ዘርፉ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ባለድርሻዎች ውስጥ አንዱና ዋናው ነው፡፡ ሆኖም ግን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት በሌሎች ዘርፎች ማለትም ለንግድና ኢንዱስትሪ፣ ለግብርናና ገጠር ልማት፣ ለጤና፣ ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይና ሌሎች የሚያስፈልገውን የአቅም ግንባታ ፍላጎት ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዋና ሚና ከሚጫወተው የንግድ ዘርፍ በተለይም በጥራት ሥራ አመራር (የሙያ ደረጃ አወጣጥ፣ ምዘና፣ ወ.ዘ.ተ) እና በትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ ዙሪያ በትብብር መሥራት

ይኖርበታል፡፡ መደበኛ ባልሆነ፣ በኢ- መደበኛና ከድርጅቶች ጋር በትብብር የሚሰጡ የትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብሮችን ጨምሮ በአገሪቱ የሚፈለጉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናዎችን እኩል ለማሳደግና ተለዋዋጭ ለሆነው የሥራ ገበያ ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የተለያዩ ዘርፎችን ፍላጎት በሚያሟላና መንግሥታዊና የግሉን ዘርፍ በሚያሳትፍ መልኩ ይዋቀራል፡፡

12.0.4 ከላይ በዝርዝር በቀረበው መሠረት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስሎች የበላይ ጠባቂነት አስተዳደራዊ ነፃነት ያለው አዲስ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት መዋቅርና አደረጃጀት በክልልና በፌዴራል መንግሥት ደረጃዎች ይዘረጋል፡፡

12.0.5 ይህም በፌዴራል ደረጃ ተጠሪነቱ ተገቢነት ላለው አካል የሆነና የራሱ ህጋዊ ሰውነት የሚኖረው የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጄንሲ ይቋቋማል፡፡ ይህ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አደረጃጀት አጠቃላይ፣ መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ትምህርትና ሥልጠና አጣጥሞ የያዘ ሥርዓት እንዲሆን ያስችለዋል። ኤጄንሲው የራሳቸውን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ህጋዊ ሰውነት በመስጠት ነፃ የአስተዳደር ሥርዓት ከመሠረቱ እንደ ፊሊፒንስ፣ ዮርዳኖስ፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ብራዚል፣ ታንዛኒያ፣ ሞሪሽየስ፣ ቦትስዋና፣ ዛምቢያና ሌሎች አገሮች ልምድን መውሰድ ተገቢ ይሆናል ፡፡

12.0.6 ኤጄንሲው በአገሪቱ የሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናዎችን ማለትም ከከፍተኛ ትምህርት በታች ያሉ ሁሉንም የሙያ ትምህርቶችና ሥልጠናዎች የማስተባበርና በዘርፉ የታቀደውን የማሻሻያ ሥራ የማካሄድ ኃላፊነት አለበት፡፡ በዚህ ረገድ የኤጄንሲው ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡

- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና ህግ ይቀርጻል፣
- ለሙያ ደረጃ አወጣጥ ደንብና ሥርዓትን ያዘጋጃል፣ብሔራዊ የሙያ ደረጃዎችን ያጸድቃል
- የክህሎት ምዘና የሚካሄድበትን ደንብና ሥርዓት ያዘጋጃል፤ አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፣ የክህሎት መመዘኛ ፈተናና ዘዴዎችን ያጸድቃል፣ የክህሎት ምዘና ፈተና መረጃ ባንክን ያስተዳድራል
- ለኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የብቃት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤ በአገር አቀፍ ደረጃ ስለሚኖረው የትምህርትና ሥልጠና ማዕቀፍ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፣

- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሥልጠና ማጠናቀቂያ ማስረጃ አሰጣጥ ሥርዓትን ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣
- ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት እውቅና አሰጣጥ ሥርዓት ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፣
- ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥራት የሥራ አመራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ይከታተላል፣
- ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሥራ ገበያ ክትትል የሚደረግበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣
- ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የፋይናንስ ደንብና መመሪያ ያዘጋጃል፤
- የግሉ ዘርፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅርቦት የበለጠ እንዲጠናከር አመቺና አበረታች ሁኔታዎችን ይፈጥራል፣
- የግልና የመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅርቦትን አቅም ለማሳደግ የሚያስችል ስትራቴጂ ይቀይሳል፣
- አስፈላጊ ምርምሮችን ያካሂዳል፤ ምርምር እንዲካሄድ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ለውጥ ተግባራዊነትን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራንን ሥልጠናና ቀጣይ ሥልጠና አፈጻጸም ይቆጣጠራል፣ የመምህራንን የቅድመ ሥራ ሥልጠናና ቀጣይ ሥልጠና ዝግጅትና አፈጻጸምን በተመለከተ የትምህርት ሚኒስቴርን ያማክራል፣
- በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት በባለድርሻዎች መካከል ሊነሱ የሚችሉ አለመግባባቶችን መፍትሔ ይሰጣል፣
- ክልላዊ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላት ተግባራቸውን እንዲወጡ እገዛ ያደርጋል፣
- የአገሪቱን የሥራ ገበያ ፍላጎት መሠረት ያደረገ፣ ተዛማጅና ለሁሉም ክፍት የሆነ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የበለጠ እንዲጠናከር ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

*የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ አንዳንድ ተግባራትን ለክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላት በውክልና ሊሰጥ ይቻላል፡፡*

12.0.7 የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ የበላይ አካል በመሆኑ ባለድርሻዎችንና የዘርፉን ተጠቃሚዎች እንዲሁም የአገሪቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶች የሚያንጸባርቅ

መሆን ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ካውንስሉ አግባብነት ያላቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ባለድርሻዎች በተለይም የግልና የመንግሥት አሠሪ ድርጅቶች ተወካዮች፣ የግል ንግድ ሥራ ዘርፍ (ንግድ ምክር ቤቶችና የግል ዘርፍ ማህበራት) ፣የግልና የመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪ ድርጅቶች፣ የሠራተኛ ተወካዮች (የሠራተኛ ማህበራት)፣ አርሶ አደሮች ፣ በገጠር ከግብርና ውጪ በሌላ ሥራ የተሠማሩ ሰዎች ተወካዮች፣ የሴቶች ተወካዮች፣ የሲቪል ማህበረሰብና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮችና የባለሙያዎች ማህበራትን ሊያቅፍ ይገባል፡፡ በካውንስሉ ውስጥ የሚወከሉ የመንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

- ትምህርት ሚኒስቴር
- አቅም ግንባታ ሚኒስቴር
- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
- የግብርና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
- የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
- የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር
- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
- የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር
- የውሃ ሃብት ሚኒስቴር
- የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር


ከዚህም በተጨማሪ የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስል ከክልል የተመረጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስል አባላትን ያቅፋል፡፡ በአጠቃላይ በካውንስሉ ውስጥ መንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት የተመጣጠነና ፍትሃዊ የሆነ የአባልነት ውክልና ይኖራቸዋል፡፡ የካውንስሉ ሰብሳቢና አባላት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሰየማሉ፡፡

12.0.8 ካውንስሉ ተግባሩን በሚገባ ማከናወን ይችል ዘንድ እንደ አስፈላጊነቱ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን ሊሰይም ይችላል፡፡ የኮሚቴ አባላት በፌዴራል ካውንስሉ በአባልነት ያልተሰየሙ ሙያተኞችን ሊያካትት ይችላል፡፡ ካውንስሉ ስብሰባዎችን ለማካሄድና ተግባራቱን ማከናወን የሚያስችል የተሟላ ጽ/ቤት ይኖረዋል።

12.0.9 የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥራ አስፈጻሚ አካል የፌዴራል ካውንስሉን ሥራ የሚያስፈጽምና ተጠሪነቱ አግባብ ላለው አካል ይሆናል፡፡ ሥራ

አስፈጻሚው በካውንስሉ የሚተላለፉ ውሳኔዎችንና መመሪያዎችን የማዘጋጀትና የማስፈጸም ሃላፊነት ሲኖረው የካውንስሉ ጽ/ቤት ሆኖ ያገለግላል፡፡ በዚህ ስትራቴጂ በተቀመጡት መርሆዎች መሠረት ሥራ አስፈጻሚው በተዋረድ የሚገኙ የዘርፉን አካላትና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጭዎች የመደገፍ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

## የፌዴራል ቴ/ሙ/ት/ሥ አስፈፃሚ አካላት




12.0.10 በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የተቀመጡ ተግባራትን ለመከናወንና ለመቆጣጠር ይቻል ዘንድ እንደ ክልሎቹ ተጨባጭ ሁኔታ በክልል ደረጃ ተመሳሳይ ወይም ተሻሽሎ የሚዋቀር ተመሳሳይ ተቋማዊ አደረጃጀት ይኖራል፡፡ የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አካላት የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል:-

- የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፖሊስና ረቂቅ ህግ መቅረጽ፣ ለክልሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ልማት ዕቅድ ማዘጋጀት፣
- በክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓትና ሌሎች የክልል ልማት ዘርፎች መካከል ተገቢ ቅንጅት መኖሩን ማረጋገጥ፣
- እንደ ክህሎት ምዘናና የትምህርትና ሥልጠና አሰጣጥ አፈጻጸም ያሉትን መቆጣጠርን ጨምሮ በክልሉ የጥራት ሥራ አመራር ሥርዓትን ማደራጀት፣
- በክልል ደረጃ ለሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሰጪ ተቋማት ዕውቅና መስጠት ፣
- በክልል ደረጃ የሥራ ገበያ ክትትል ማካሄድና የክልሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዕቅድ የክትትል ውጤቱን በመጠቀም መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣
- ክልላዊ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የፋይናንስ ደንብና መመሪያ ማውጣት፣

- በክልል የግሉ ዘርፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እንዲጠናከር አመቺና አበረታች ሁኔታዎችን መፍጠር፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን አቅም መገንባት፣
- የክልሉን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አቅርቦት ዕቅድ ማውጣትና አፈፃፀሙን መቆጣጠር፣
- ክልላዊ የሙያ ደረጃ ምደባዎችን ማዘጋጀት፣
- የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲን በመወከል የሙያ ምዘና ማካሄድና የሙያ ምዘና ማስረጃ መስጠት፣
- በክልሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት አሠሪዎች የሚሳተፉበትን ተገቢ ስትራቴጂ መቀየስ፣
- ጥናትና ምርምሮችን ማካሄድ፣ ምርምር እንዲደረግ ማድረግ፣ ቁጥጥር ማካሄድ፣
- በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ሥርዓት በባለድርሻዎቹ መካከል ሊነሱ የሚችሉ አለመግባባቶችን መፍታት፣
- በዞንና በወረዳ ደረጃ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላትን ኃላፊነት መወሰንና ድጋፍ መስጠት፣
- በክልል ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አፈጻጸምን መቆጣጠር ፣
- ክልላዊ የሥራ ገበያ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ፣ ተዛማጅና ለሁሉም ክፍት የሆነ የቴክኒካና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የበለጠ እንዲጠናከር ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን ማከናወን፡፡

12.0.11 ክልላዊ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላት የተለያዩ ባለድርሻዎችን ያካተተ የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ካውንስል ይኖራቸዋል። የክልሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈጻሚ አካል የካውንስሉ አስፈጻሚ አካል ሆኖ የዕለት ተዕለት ሥራውን ያስፈጽማል፡፡ የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላት የሥራ ቢጋር ፣ ተግባር ፣ ኃላፊነትና መዋቅር በዚህ ስትራቴጅ በተቀመጡ መርሆዎችና አግባብነት ያላቸው የህግ ሰነዶች መሠረት በክልሉ መንግሥት የሚወሰን ይሆናል፡፡ አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂ የክልሉን የሥራ ገበያና ኢኮኖሚ አቅጣጫ ተከትሎ ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ የክልል መንግሥታት የየራሳቸውን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂ እንዲቀርጹ ይበረታታሉ፡፡

12.0.12 ባልተማከለ አሠራር መርህ መሠረት ዋና ዋና የሥራ ኃላፊነቶች ወደ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት እንዲወርዱ ይደረጋል፡፡ ወደፊት የመንግስት

ተቋማትን አስመልክቶ ባለው የአገሪቱ ህግ ማዕቀፍ መሠረት የመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በፋይናንስ ሥራ አመራር ፣ በትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብር እቅድና ዝግጅት ፣ በሥርዓተ ትምህርት ማሻሻያና በመሳሰሉት ሰፊ የውስጥ አመራር መብት (autonomy) እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ የህዝብ ሀብትና ንብረት አላግባብ መጠቀምን ለማስወገድና የተቋማት ዕቅድ ከአካባቢው ማህበረሰብ የሥራ ገበያ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም ይህ ተጨማሪ ኃላፊነት ጠንካራና አቅም ያለው አመራርና ቁጥጥር ያስፈልገዋል፡፡ በመሆኑም የቴክኒክና ሙያ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ሥራ አመራር ቦርድ አባላት ከዘርፉ ባለድርሻዎች ከዋና ዋና የመንግሥትና የግል ድርጅቶች የተውጣጡ ሆነው በአካባቢው የሚገኙ የንግድ ህብረተሰብ አባላት ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፣ የጥቃቅን ብድርና ፋይናንስ ተቋማት፣ ሲቪል ማህበረሰብ፣ ግብርናና ገጠር ልማት ፣ ትምህርት፣ ንግድና ኢንዱስትሪ (የክልል መካከለኛና አነስተኛ የንግድ ሥራ ድርጅቶች) እና ሌሎቹም አግባብነት ያላቸው የመንግሥት አካላት የሚወከሉበት ይሆናል፡፡ የሥራ አመራር ቦርዱ ተቋማትን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፡፡ የተቋማትን በጀት፣ የሥራ እቅድና ዓመታዊ ሪፖርት ያጸድቃል፤ ከተቋማቱ ሥራ አመራርና የቴክኒክና ሙያ የትምህርትና ሥልጠና አፈጻጸም ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ አጠቃላይ ምክር ይሰጣል፡፡ የሥራ አመራር ቦርዱ አባላት ተቋማቱ ተጠሪ በሆኑበት ባለሥልጣን የሚሰየሙ ሲሆን፣ የቦርዱ ተጠሪነትም ለባለሥልጣኑ ይሆናል፡፡

# 13. ስለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ግንዛቤ መፍጠር

13.0.1 እንደሌሎች ብዙ የአፍሪካ አገሮች ሁሉ በአገራችን ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ያለው አመለካከት ዝቅተኛ ነው፡፡ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ያለው አመለካከት አድካሚና ዝቅተኛ ሥራ፣ ዝቅተኛ ደመወዝ እንዲሁም ለሠልጣኙ የዕድገት ዕድል የሌለው ተደርጎ ነው፡፡ የዚህ አመለካከት መነሻም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ምሩቃንን በሥራው ገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችላቸው ጥራት ያለው የትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብር አለመኖር ነው። የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግባት ያልቻሉና አማራጭ የሌላቸው ተማሪዎች መግቢያ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ይህ አመለካከት መቀየር ይኖርበታል፡፡

13.0.2 በመሆኑም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈፃሚ አካላት ከባለድርሻዎች በተለይም ከንግድ ሥራ ድርጅቶች ጋር በመሆን በመጀመሪያ ከቀጥተኛ ባለድርሻዎች ቀጥሎም ህብረተሰቡ በአጠቃላይ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት በሥራ ገበያ ፍላጎት መሠረት ጥራት ያለው ትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብር የሚቀርብበትና የሙያ ብቃት የሚገኝበት ሁኔታ እየተመቻቸ መሆኑ፣ የትምህርትና ሥልጠና ዕድል

በገጠርና በከተማ ለሚገኙ ማንኛውም ወገን ክፍት መሆኑንና ግልፅ የሆነ የትምህርት ደረጃና የሙያ ዕድገት ዕድሎችን የያዘ መሆኑን ለማሳወቅ በግንዛቤ ፈጠራ ሥራ ላይ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ አሠሪዎችና የግል የንግድ ሥራ ዘርፍ ባለቤቶችም ስለሁኔታው ግንዛቤ እንዲኖራቸውና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ባለቤት እንዲሆኑ ለማድረግ ልዩ ጥረት ይደረጋል፡፡

13.0.3 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ገጽታን ለማሻሻልና ለማሳደግ በአገር ውስጥ የሙያ ውድድር እንዲስፋፋና ኢትዮጵያውያን በዓለም አቀፍ የሙያ ውድድሮች ላይ እንዲሳተፉ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ።

# 14. የዓለም አቀፍ ትብብር ሥራዎችን መምራት

14.0.1 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓትን በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይንና ሙያን የሚጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም መንግሥት አጋር አገሮች ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የቴክኒክና ፋይናንስ ድጋፋቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ ያደርጋል፡፡ ሆኖም ግን የሚቀርቡ የትብብር ፕሮጀክቶች ለዘርፉ ፍላጎት ምላሽ የሚሰጡና በዚህ ዶክሜንት የተዘረዘሩ ዓለማዎችንና መርሆዎችን የተከተሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

14.0.2 በክልልና በፌዴራል መንግሥት ደረጃ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና  አስፈጻሚ አካላት ማናቸውም ከአንድ ወይም ከተለያዩ ወገኖች ጋር የሚደረጉ የሁለትዮሽና የባለብዙ ወገን ትብብሮች በዚህ ስትራቴጂ ውስጥ የተቀመጡ ዓላማዎችን ለማሳካት እንዲሁም ከዘርፉ ዓመታዊና የአምስት ዓመት ሥራ ዕቅድ ጋር የተቀናጁ መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡ የተቀናጀ አካሄድ እንዲኖርና የሚቃረኑ ወይም የሚደራረቡ ሥራዎችን ለማስወገድ ከለጋሾች ጋር ስለሚኖር ትብብር ተገቢው የአሠራር ስልት ይቀየሳል፡፡ በዘርፉ የሚኖሩ የትብብር ፕሮጀክቶች ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ከአገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ጋር የሚጣጣም መሆን ይኖርበታል፡፡